በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌደራል
ዋና ኦዲተር መ/ቤት

# በግብርና ሚኒስቴር
# በደን ሀብት ልማት እና አጠባበቅ

## ላይ
## የተከናወነ የክዋኔ እና የአካባቢ
## ኦዲት ሪፖርት








ሐምሌ 2004 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# ማውጫ


**መግቢያ ........ 1**

የግብርና ሚኒስቴር መ/ቤት ዓላማ፣ ስልጣንና ተግባር ........ 3

*የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማ፤ ........ 3*

*የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር፤ ........ 3*

የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ........ 5

*ድርጅታዊ መዋቅር ........ 5*

*የሰው ኃይል ........ 5*

የመ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ........ 5

**የኦዲቱ ዓላማ ........ 6**

**የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ ........ 6**

**ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (POTENTIAL AUDIT AREA) ........ 7**

**የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (AUDIT ISSUES) ........ 7**

**የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (AUDIT EVALUATIVE CRITERIA) ........ 8**

**የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሥራ ሂደት መግለጫ /PROCESS DESCRITPTION/ ........ 8**

**የኦዲት ግኝቶች ........ 11**

የደን ፖሊሲ፣ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን በተመለከተ ........ 11

የደን ልማት፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀምን የሚመለከቱ ተግባራት በዕቅድ ተካተው የሚተገበሩ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 12

**የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መዘጋጀትን በተመለከተ፤ ........ 13**

የጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ልማት፣ አጠባበቅና አጠቃቀምን በተመለከተ ........ 15

*የጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ልማትን በተመለከተ፤ ........ 15*

*የጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ጥበቃ እና ቀጣይነት ያለው አጠቃቀምን በተመለከተ፤ ........ 16*

ቅድሚያ የተሰጣቸው የሀገሪቱ ጥብቅ የተፈጥሮ ደኖች አስተዳደርን በተመለከተ፤ ........ 16

ለጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች ተገቢው ጥበቃ የሚደረግላቸው መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 18

ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎችን ከድንገተኛ እሳት ቃጠሎ መከላከልን በተመለከተ፤ ........ 22

የደን ሀብት መቆጣጠሪያ ኬላ ማቋቋምን በተመለከተ፤ ........ 24

*ለልማት ተግባር የሚሰጡ ቦታዎች በተፈጥሮ ደን ሀብቱ ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩ ማድረግን በተመለከተ፤ ........ 25*

*ስለደን ሀብት ጠቀሜታ እና አጠባበቅ ግንዛቤ መስጠትን በተመለከተ፡፡ ........ 27*

ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቱን በመጠበቁ ረገድ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላላቸው ባለድርሻ አካላት ........ 27

ሀ/ ስለደን ሀብት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ግንዛቤ መስጠትን በተመለከተ፤ ........ 27

ለ/ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ቀጣይነትን በተከተለ ሁኔታ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማግኘት ላይ ግንዛቤ መስጠትን በተመለከተ ........ 29

ሐ/ የደን እሳት መከላከልን በተመለከተ ተግባራዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ የተሰጠ መሆኑን በተመለከተ፤ ........ 31

በአጠቃላይ ለሀገሪቱ ኅብረተሰብ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ጠቀሜታን በተመለከተ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠትን በተመለከተ ........ 33

የደን ሀብትን የሚመለከቱ መረጃዎች አደረጃጀት እና ልውውጥን በተመለከተ ........ 34

*የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚያስችል ሥርዓትን በተመለከተ፤ ........ 34*

*ለደን ልማት ተግባር በተከለሉ አካባቢዎች ላይ የተተከሉ ችግኞችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በተመለከተ ........ 35*

*የደን እሳት አደጋ ክስተትና መከላከል መረጃ ልውውጥን በተመለከተ ........ 37*

በደን ሀብት ዙሪያ ሊከናወኑ የሚገቡ ተግባራትን ለማከናወን ያለውን አደረጃጀትና የሰው ኃይልን በተመለከተ ........ 38

*አጠቃላይ አደረጃጀት እና የሰው ኃይልን በተመለከተ፤ ........ 38*

*የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መረጃ የሚያቀነባብሩና የሚያሰራጩ አካላት በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች መጠናከራቸውን በተመለከተ* ........ *40*
በደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ላይ የግል ባለ ሀብቱን እና ሌሎች የህረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎን በተመለከተ ........ 41
**መደምደሚያ ........ 42**
**የማሻሻያ ሀሳብ ........ 44**
**አባሪዎች ........ I**
PERCENTAGE OF COUNTRY FOREST COVERAGE DURING THE 20TH CENTURY ........ I
HUMAN IMPACT ON FORESTS IN ETHIOPIA FROM 1973 TO 1990 ........ I
የፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር መ/ቤት መዋቅር ........ II
የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (AUDIT EVALUATIVE CRITERIA) ........ III
ለግብርና ልማት ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ የተሰጠ የመሬት ስፋት እና የወሰዱ ባለሀብቶች ብዛት ........ VI
SOME OF THE MAJOR RECENTLY ALLOTTED FOREST AREAS FOR INVESTMENTS IN PLANTATION IN SHEKA ZONE ........ VI
IUCN CATEGORIES OF PROTECTED AREAS ........ XIII

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ደን ተፈጥሮአዊ እና ሰው ሠራሽ በሚል በሁለት የሚከፈል ሲሆን፣ ተፈጥሮአዊ ደን በተፈጥሮ የበቀሉ የተለያዩ የዛፍ ዝርያዎች፣ ቁጥቋጦና ሌሎች የእንጨትነት ፀባይ ያላቸው ተክሎች የበቀሉበት እና ከፍተኛ የብዝሀ ህይወት ክምችት የሚገኙበት ነው፡፡ የተፈጥሮ ደን አካባቢዎች መኖር የሥነ-ምህዳራዊ (ecosystem) ጤንነትን እና ከፍተኛ ብዝሀ ህይወት ስብጥር እና ክምችትን በመጠበቅ የአካባቢ ንብረት መለወጥን (climate change) በመከላከሉ ረገድ የማይተካ ሚና ከመጫወታቸው በተጨማሪ ሰፊ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ስላላቸው ድህነትንም ለመቀነስ ሰፊ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ሆኖም ለነዚህ የተፈጥሮ ደኖች የሚደረገው ጥበቃ አጥጋቢ ባለመሆኑ ወደ ሌላ የመሬት አጠቃቀም እየተለወጡ በከፍተኛ ሁኔታ በመመናመን ላይ ይገኛሉ[1]፡፡

2. በዓለም አቀፍ ደረጃ የደን ሀብት መመናመን በአካባቢ፣ በኢኮኖሚ እና በማኅበረሰብ ላይ እያስከተለ ያለውን ተጽዕኖ ለመግታት ሰፊ ጥረት እየተደረገ ሲሆን፣ በአለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በዓለም አቀፍ ደረጃ ሀገራት የደን ሀብትን በማልማት እና በመጠበቅ ዙሪያ የተዘጋጁ ስምምነቶችን በመቀበል እንደራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ቃል ገብተዋል፡፡ ሀገራችንም የብዝሀ ሕይወት ጥበቃ ስምምነትን ጨምሮ ሌሎች ከደን ሀብት ጥበቃ ጋር የተያያዙ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ተቀብላለች፡፡

3. ከዋልታ አካባቢዎች ወደ ምድር ወገብ እየተቀረበ በሄደ ቁጥር የተፈጥሮ ደን የብዝሀ ሕይወት ስብጥር መጠን እየጨመረ እንደሚሄድ በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ይገልፃሉ፡፡ ሀገራችን ለደን ሀብት ልማት ምቹ ከመሆንዋም በላይ በምድር ወገብ አቅራቢያ የምትገኝ በመሆኗ የተፈጥሮ ደን ሀብቶቿ ከፍተኛ የብዝሀ ህይወት ስብጥር ይታይባቸዋል፡፡ በመሆኑም በዓለም ከፍተኛ የብዝሀ ሕይወት ስብጥር እና ሀብት ካላቸው ሀገራት መካከል የምትመደብ ከመሆኗም በላይ በሌላው ዓለም የማይገኙ (endemic) በርካታ የዕጸዋት እና የእንስሳት ዝርያዎች ይገኙባታል፡፡

[1] Forest Decline and Its Causes in the South-Central Rift Valley of Ethiopia: Human Impact over a One Hundred Year Perspective- Gessesse Dessie and Carl Christiansson

4. የደኑ ዘርፍ ለአካባቢው ኅብረተሰብ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያዎች ለሚቀርቡ የደን ውጤቶች ግብአት በመሆን እራሱን ችሎ ሊንቀሳቀስ እና የሀገርን ኢኮኖሚ ሊደጉም እንደሚችል በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች ይገልፃሉ[2]። ሆኖም በሁኔታዎች አለመመቻቸት ሀገራችን ከዚህ ዘርፍ የሚጠበቀውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ተፈጥሮአዊ ጥቅም ሊገኝ የሚችለውን ያህል እያገኘች እንዳልሆነ መረጃዎች ያስረዳሉ።

5. ሆኖም ያላት የተፈጥሮ ደን ሀብት ይዞታ ከ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ በተለያዩ ተፅዕኖዎች ምክንያት  በከፍተኛ ሁኔታ ተመናምኗል። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ከመጣው የሀገሪቱ የሕዝብ ቁጥር ጋር በተያያዘ ለእርሻ መሬት፣ ለመኖሪያ ቦታ፣ ለማገዶ፣ ለኮንስትራክሽን እና ለሌሎች ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴዎች እየዋለ ስለመጣ የሀገሪቱ የደን ይዞታዎች መጠን በከፍተኛ ሁኔታ እየተመናመነ ይገኛል። በ20ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ አካባቢ 35 በመቶ የነበረው የሀገሪቱ የተፈጥሮ ደን ሽፋን በ20ኛው ምዕተ ዓመት መገባደጃ ላይ ወደ 2.3 - 3 በመቶ (113 ሚሊየን ሄክታር) የወረደ ሲሆን (አባሪ 1)፣ ይህ አስከፊ ገጽታ በወቅቱ በዓመት 169 000 ሄክታር የተፈጥሮ ደን የሚመነጠር እንደነበር ያሳያል[3]። በአሁኑ ወቅት የተፈጥሮ ደን በአብዛኛው በሀገሪቱ ደቡብ እና ደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ብቻ የሚገኝ ሲሆን፣ ይህም ሊተርፍ የቻለው በቀላሉ ሊደረስባቸው በማይቻሉ ብዙ ህዝብ ባልሰፈረባቸው አካባቢዎች የሚገኝ በመሆኑ ነው[4]።

6. በቅርቡ የወጡ መረጃዎች የሀገሪቱ አጠቃላይ የደን ሽፋን እየጨመረ መምጣቱን የሚገልጽ ቢሆንም የሀገሪቱ የተፈጥሮ ደን ሀብት ሁኔታን በተመለከተ የኦዲት ቡድኑ በመስክ ጉብኝት ከተመለከተው እና ከሰበሰባቸው መረጃዎች አንጻር ሲታይ ከብዝሀ ህይወት ሀብት ስብጥር አ|ኳያ የጎላ ጠቀሜታ ያላቸው የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ተገቢው ጥበቃ እየተደረገላቸው አይደለም።  ከዚህም በተጨማሪ ይህንን

[2] National Consultation Meeting on Research and Development of Non Timber Forest Products in-page,3 Ethiopia, 2009

[3]Environmental Low of Ethiopia, Girma Hailu- Regional Environment Especialist

[4]**WORKSHOP ON TROPICAL SECONDARY FOREST MANAGEMENT IN AFRICA: *Reality and perspectives  In collaboration with ICRAF and CIFOR Nairobi, Kenya, 9-13 December 2002***

ውድ የተፈጥሮ ሀብት በተቀናጀ ሁኔታ ለመጠበቅ እንዲቻል 4.8 ሚሊየን ሄክታር[5] የቦታ ስፋትን የሸፈኑ 58 ጥብቅ የተፈጥሮ ደን አካባቢዎች ከሶስት ምዕተ አመታት በፊት የተለዩ ቢሆንም ለዚህ ውድ የተፈጥሮ ሀብት የሚደረገው ጥበቃ እና ልማት ዝቅተኛ እንደሆነ የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ[6]፡፡

7. የሀገሪቱ የደን ሀብትን የማልማት፣ የመጠበቅ አና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ጥቅም ላይ የማዋል ልምድ እንዲዳብር የማድረግ ተግባርን የማከናወን ኃላፊነት በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ አካላት ሥር በተለያየ ደረጃ እና አደረጃጀት ተዋቅሮ እንዲከናወን ተደርጓል፡፡ ሆኖም ይህ በጥቅሉ ሲታይ መረጋጋት የሌለበት እና ቢያንስ ለ13 ጊዜያት እንዲቀያየር የተደረገ በመሆኑ ይህ ሁኔታ የደን ሀብቱን በአግባቡ ለማስተዳደር እና ሀገሪቱም ከዚህ ሀብት የሚፈለገውን ያህል ተጠቃሚ እንዳትሆን እንዳደረጋት በሀገሪቱ የደን ሀብት ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ይገልጻሉ፡፡ ይህ ኦዲት በተከናወነበት ወቅት የሀገሪቱን የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ተግባር በግብርና ሚኒስቴር መ/ቤት እየተከናወነ ይገኛል፡፡

# የግብርና ሚኒስቴር መ/ቤት ዓላማ፣ ስልጣንና ተግባር

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማ፤

8. የደን ሀብትን በተመለከተ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዋናው ዓላማ የሀገሪቱን የደን ሀብት በአግባቡ በማልማት የህብረተሰቡን የደን ውጤቶች ፍላጎት ማሟላትና በአግባቡ በመጠቀም የሀገሪቱ የደን ሀብት ለኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዲያበረክት ማድረግ ነው፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ህብረተሰቡን ከድህነት የሚያላቅቅ፣ የላቀ ቴክኖሎጂ የሚጠቀምና ከፍተኛ ምርትና ምርታማነት ደረጃ የደረሰ፣ ለኢኮኖሚ መዋቅራዊ ለውጥ መሠረት መጣል የሚያስችል ዘመናዊ የግብርና ሥርዓት መፍጠር ሌላው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዐብይ ዓላማ ነው፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር፤

9. በሚኒስቴር መ/ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 691/2003 መሠረት መ/ቤቱ የተፈጥሮ ሀብት በዘላቂ የግብርና ልማት የሚጠበቅበትንና የሚለማበትን ስልት የመቀየስ እና

[5] ከዚህ ዉስጥ 2.8 ሚሊየን ሄክታር በተፈጥሮ ደን ፣ 0.1ሚሊየን ሄክታር ለአንደስት አገልግሎት በተተከለ ደን የተሸፈነ ሲሆን፣ ቀሪው1.9 ሚሊየን ሄክታር ደግሞበደን ያልተሸፈነ እና ለእርሻ ተግባር እየዋለ ያለ ነው፡

[6] WORKSHOP ON TROPICAL SECONDARY FOREST MANAGEMENT IN AFRICA: Reality and perspectives In collaboration with ICRAF and CIFOR Nairobi, Kenya, 9-13 December 2002

ተግባራዊ የሚሆንበትን ሁኔታ የማመቻቸት እንዲሁም በግብርና ምርት ላይ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ወቅታዊ ሁኔታዎችን የመከታተል እና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት የመዘርጋት ተግባራትን የሚያከናውን ሲሆን፣ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን በተመለከተ በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና በአዋጅ ቁጥር 542/1999 መሠረት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚከተሉትን ስልጣንና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡

- የፌዴራልና የክልል ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር እና አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ በመስጠት በዚሁ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መፈፀማቸውን ያረጋግጣል፣
- በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ሥራዎችን በመከታተልና በመገምገም የሚገኙ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ አዳዲስ የፖሊሲ ሀሳቦች እንዲነደፉና አስፈላጊም ሲሆን በሥራ ላይ ያለው ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም ሕግ እንዲሻሻል ያደርጋል፣
- በደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም ዙሪያ ያሉትን ሀገር በቀልና የውጭ ዕውቀቶች፣ ልምዶች እና ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችሉ የደን ቴክኖሎጂ ፓኬጆችን በማዘጋጀት የደን አልሚውን ዕውቀትና ክህሎት እንዲያድግ የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፡፡
- በሀገሪቱ ስለሚገኝ ወቅታዊ የደን ሁኔታ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል አካላት ጋር የማያቋርጥ የመረጃ ልውውጥ መረብ እንዲኖር ያደርጋል፣
- የሀገሪቱ የደን ልማት የሀገር ውስጥ ፍጆታን በመሸፈን የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ የደን ውጠቶችን ለውጭ ሀገር ገበያ ለማቅረብ እንዲቻል ወቅታዊ ሁኔታዎችን በመከታተል ለክልሎች የቴክኒክ ድጋፍና እገዛ ያደርጋል፡

10. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ አንድ (1) መሠረት በሀገር ውስጥ ያሉት ሁሉም ክልሎች በክልላቸው ውስጥ የሚገኝን ማንኛውንም የመንግስት ደን የማስተዳደር ኃላፊነት እና ስልጣን ያላቸው ቢሆንም፣ ደኑ በሚገኝባቸው አጎራባች ክልሎች በጋራ በአግባቡ ሊጠበቅና ሊለማ ያልቻለበት ሁኔታ ሲፈጠር፣ ደኑ በሚገኝበት ክልል ጠያቂነት ወይም ከደኑ ሀገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጠቀሜታ አንፃር

በሚኒስቴሩ ሥር ሆኖ መተዳደር የሚኖርበት ሁኔታ ሲፈጠር ሚኒስቴሩ ደኑን ተረክቦ እንዲያስተዳድረው ሊደረግ ይችላል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የሰው ኃይል ድርጅታዊ መዋቅር

11. በሚኒስቴር መ/ቤቱ በተካሄደው የመሠረታዊ የአሠራር ሥርዓት ለውጥ ጥናት (BPR) መሠረት ሚኒስቴር መ/ቤቱ በአንድ ሚኒስትር የሚመራ ሲሆን፣ ለሚንስትሩ ተጠሪ በሆኑ ሶስት ሚኒስቴር ዴታዎች የሚመሩ ሦስት ዋና ዋና ዘርፎች ማለትም የተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ፣ የግብርና ልማት ዘርፍ እና የአደጋ መከላከልና ዝግጁነትና የምግብ ዋስትና ዘርፍ አሉት፡፡ የተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ እና የአደጋ መከላከል፣ ዝግጁነትና የምግብ ዋስትና ዘርፍ እያንዳንዳቸው በሁለት ሁለት የሥራ ሂደቶች (ዳይሬክቶሬቶች)፤ የግብርና ልማት ዘርፍ ደግሞ በአራት የሥራ ሂደቶች (ዳይሬክቶሬቶች) ተደራጅተዋል፡፡ በእነዚህ በሶስት ዞርፎች ስር የተዋቀሩ ስምንት ዳይሬክቶሬቶች የመ/ቤቱ ዋና ዓላማ አስፈፃሚ ሲሆኑ፣ ከነዚህ በተጨማሪ ስምንት ደጋፊ የሥራ ሂደቶች እንዲሁም አንድ የሕዝብ ግንኙነት ቢሮ እና አንድ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማኔጅመንት ማዕከል ሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲኖረው ተደርጎ ተደራጅቷል፡፡ የደን ልማት እና ጥበቃን ተግባር የሚያከናውን አካል በተፈጥሮ ሀብት ዘርፍ በተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ዳይሬክቶሬት ስር በኬዝ ቲም ደረጃ (በቡድን ደረጃ) በአምስት የሰው ኃይል ተዋቅሯል (አባሪ 1)፡፡

## የሰው ኃይል

12. ኦዲቱ በተከናወነበት ወቅት በሚኒስቴር መ/ቤቱ በአጠቃላይ 1428 ሠራተኞች ሲኖሩት፣ ከዚህ ውስጥ 123 ሠራተኞች በጊዜዊነት የሚሠሩ ናቸው፡፡ የሠራተኞቹ የትምህርት ደረጃ ሲታይ 12 (0.8%) ሶስተኛ ዲግሪ፣ 47 (3.2%) ሁለተኛ ዲግሪ፣ 135 (9.4%) የመጀመሪያ ዲግሪ፣92 (6.4%) ዲፕሎማ፣ እንዲሁም 1142 (80.2%) የሚሆኑ ሠራተኞች ከዲፕሎማ በታች ያላቸው ናቸው፡፡

## የመ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

13. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተጣለበትን የሥራ ኃላፊነት ለማከናወን የሚያስፈልገውን ገንዘብ ከመንግስት ከሚመደብ በጀት እንዲሁም ከብድርና ከዕርዳታ ምንጮች ያገኛል፡፡ ከብድር እና ከዕርዳታ ምን ያህል ገንዘብ እንዳገኘ የተሟላ መረጃ ማግኘት ስላልተቻለ

ለመግለጽ አልተቻለም፡፡ በ2000፣ በ2001፣ በ2002 እና በ2003 በጀት ዓመታት እንደ ቅደም ተከተሉ ብር 2.34፤ 2.38፤ 2.43 እና 2.4 ቢሊዮን ብር ከመንግሥት በጀት የተመደበለት ሲሆን፣ ከዚህ ወስጥ ከላይ በተጠቀሱት አመታት ሥራ ላይ የዋለው እንደ ቅደም ተከተሉ ብር 2.17፣ 1.79፣ 2.26፣ እና 2.21 ቢሊዮን (በመቶኛ ሲገለጽ 92.6%፣ 75.28%፣ 92.75% እና 90.81%) መሆኑ ታውቋል፡፡

# የኦዲቱ ዓላማ

14.የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የግብርና ሚኒስቴር የሀገሪቱን የተፈጥሮ የደን ሀብት ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ፣ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማልማት፣ ለመጠበቅ እና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ የተደረገ መሆኑን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ካሉ በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦች ለማቅረብ ነው፡፡

# የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

15.ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በግብርና ሚኒስቴር ሲሆን፣በዋናነት ያተኮረው ደግሞ ባለፉት አራት ተከታታይ የሥራ ዓመታት (ከ2000 እስከ 2003 ዓ.ም) በሚኒስቴሩ በተከናወኑ ሥራዎች ላይ ነው፡፡ ኦዲቱ የተከናወነው የደን ሀብት ልማትና ጥበቃን በተመለከተ ተያያዥ የሆኑ መረጃዎችን ማለትም በሚኒስቴር መ/ቤቱ የወጣውን የደን ሀብት ልማት፤ ጥበቃ፣ አጠቃቀም ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና አዋጅን፤ ያለፉትን የሶስት ዓመት የሚኒስቴር መ/ቤቱን የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶችን፣ እንዲሁም በተለያዩ ባለሙያዎች የደን ሀብትን በተመለከተ የተጠኑ ጥናቶችን በመከለስ፤ በናሙና የተለዩ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን አካባቢዎችን በአካል በመጎብኘት እና በአካል በመስክ ላልታዩ ክልሎች መጠይቅ በመላክ ነው፡፡

16.ከዚህም በተጨማሪ በተፈጥሮ ደን ልማት፣ጥበቃ እና አጠቃቀም ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ የሆኑ እና ያልሆኑ ድርጅቶችን የሥራ ክንውን የሚገልጹ መረጃዎችን በመከለስ እና ቃለ መጠይቅ በማቅረብ ለኦዲት ሥራው አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን የተሰበሰቡ ሲሆን፣በመቀጠልም ከሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በናሙና ከተመረጡ ባለድርሻ አካላት ከተሰበሰቡ መረጃዎች መካከል ማብራሪያ ለሚያስፈልጋቸው ነጥቦች

ለሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ የተገኙ መረጃዎችን የማጠናከር ሥራ ተከናውኗል።

17. በኦዲቱ ወቅት በናሙና በተመረጡ በአምስት የፌዴራል ባለድርሻ መ/ቤቶች፤ በሁለት ክልሎች የሚገኙ የግብርና ቢሮዎች እና ዘጠኝ ለጥበቃ የተከለሉ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን አካባቢዎችን በአካል ተጎብኝተዋል። በተጨማሪም በተፈጥሮ ደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ባለድርሻ የሆኑ 4 መንግስታዊ እና 5 መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እንዲሁም በአካል በመስክ ባልተጎበኙ ክልሎች የሚገኙ የግብርና ቢሮዎች መጠይቅ በመላክ በኦዲቱ ለመዳሰስ ተሞክሯል።

# ለክዋኔ ኦዲቱ የተለየው የኦዲት አካባቢ (Potential Audit Area)

18. ከላይ የተመለከቱትን የኦዲት ዘዴዎችን በመጠቀም የተሰበሰቡትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ በሀገሪቱ የደን ሀብት ዙሪያ እየታዩ ያሉትን ችግሮች በማገናዘብ ለዝርዝር ኦዲት የተመረጠው የኦዲት አካባቢ "የሀገሪቱ የተፈጥሮ እና የተተከለ የደንሀብት ኢኮኖሚያዊ በሆነ ሁኔታ፣ በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ እየለማ፣ እየተጠበቀ እና ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑን መገምገም" የሚል ነው።

# የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

19. ከላይ በተገለጸው የኦዲት አካባቢ ስር ሁለት የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) የተመረጡ ሲሆን፣ ለአንደኛው የትኩረት አቅጣጫ ሁለት ንዑስ የትኩረት አቅጣጫ ተቀምጦለታል። እነርሱም፡-

1- የሀገሪቱን የደን ሀብት በብቃትና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠበቅ እና ለማልማት የሚያስችል የአሠራር ሥርዓትየተዘረጋና ተግባራዊ የሆነ መሆኑን ማረጋገጥ፤

1.1 የሀገሪቱን የደን ሀብት በብቃትና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠበቅ እና ለማልማት የተዘረጋ የአሠራር ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ፤

1.2 በመንግስት ይዞታ ስር የሚጠበቁ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ልማት እና ጥበቃ በተዘረጋው የአሠራር ሥርዓት መሠረት እየተከናወኑ መሆኑን ማረጋገጥ

2-የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን በተመለከተ የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተዘረጋ እና በብቃት ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ማረጋገጥ፤

የሚሉ ናቸው፡፡

## የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria)

20.የደን ልማት፤ ጥበቃና አጠቃቀም ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና አዋጅ፤ በደን ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶች፤የመንግስት የአምስት ዓመታት የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዝርዝር ዕቅድ፤የሚኒስቴር መ/ቤቱ የተፈጥሮ ሀብት መሠረታዊ የስራ ሂደት ጥናት፣ ከ2000 እስከ 2003 ላሉት የአራት ዓመታት የተዘጋጁ ዕቅዶች እና የዕቅድ ክንውን ሪፖርቶች፤እንዲሁም መልካም ተሞክሮዎችን መሠረት በማድረግ በኦዲት ቡድኑ ለተመረጡት ሁለት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 19 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች የተዘጋጁ ሲሆን፣ የዝርዝር ኦዲቱም እነዚህን የኦዲት መስፈርቶች መሠረት በማድረግ ተከናውኗል፡፡ የመመዘኛ መስፈርቶች በአባሪ 3 ተያይዘዋል፡፡

## የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም የሥራ ሂደት መግለጫ /Process Description/

21.የደንልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ደረጃ በደረጃ የሚከናወኑ ተግባራት ሲሆኑ፣ የአሠራር ሂደቱ የሚጀመረው ቀደም ሲል በተሰባሰቡት መረጃዎች መሠረት በተመረጠ ተፋሰስ ውስጥና ውጪ የተጠቃሚውን ኅብረተሰብ ፍላጎት በመለየት እና የክልሎችን ፍላጎት የያዘ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድን መሠረት በማድረግ ደኖችና የደን መሬቶችን ለመከላከልና ለመቀየስ ቅድመ ዝግጅት ተደርጎ የደን ክለላ፣ ቅየሳና ምዝገባ ሥራ በፌደራል ባለሙያዎች ድጋፍ ከክልሎች፤ ከዞንና ከወረዳ ባለሙያዎች ጋር በመሆን የሚከናወን ሲሆን፣ ከዚህ ጋር በማያያዝ በተመረጡ የደን ቦታዎች በመስክ በመገኘት ለደን ማኔጅመንት ፕላን ዝግጅት የሚያስፈልጉ የደን ክለላና ቅየሳ፣ የደን ምዝገባና የማህበራዊ ምጣኔ ሀብት መረጃዎችን የማሰባሰብ ተግባር ይከናወናል፡፡ ከዚህ መረጃ የማሰባሰብ ሥራ በተጓዳኝ ስለደን ማኔጅመንት ዝግጅት በህብረተሰቡ ዘንድ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራም ይከናወናል፡፡

22. ለደን ክለላ፣ ቅየሳና ምዝገባ ሥራ የተሰባሰቡት መረጃዎች ከተተነተኑ በኋላ የጥበቃ ስራ የሚያስፈልጋቸውን፣ የደን ልማት የሚካሄድባቸውን እና ለጥቅም የደረሱ ደኖችን ስፋትና መጠን በመለየት የደን ማኔጅመንት ፕላን ይዘጋጃል፡፡ የተዘጋጀው የደን ማኔጅመንት ፕላን የሚመለከታቸው የክልል ባለሙያዎች እና አግባብነት ያላቸው አካላት በተገኙበት ዐውደ ጥናት አስተያት ከተሰጠበት በኃላ ከውይይቱ የተገኙትን ጠቃሚ ሀሳቦች በማካተት እንዲዳብር ይደረጋል፡፡በቀጣይ ይህንን የደን ማኔጅመንት ፕላን መሠረት በማድረግ በመንግስት፣ በህብረተሰቡና በግል የደን ልማት የሚካሄድባቸው የልማት ይዞታዎችን መለይትና ካርታ ማዘጋጀት የሚከናወን ሲሆን፣ እንደአስፈላጊነቱ በደን ይዞታዎች ላይ ለሚከናወኑ ተከላዎች ዘር የማዘጋጀት፣ የሚፈለገውን የዛፍ ችግኝ አይነትና መጠን መሟላት የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት እና ለተሳታፊዎች የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት በዋናነት የሚከናወኑ ተግባራት ናቸው፡፡በቀጣይ የተዘጋጁትን ችግኞች ተከላ፣የተተከሉት ችግኞች ለተባለለት የልማት ግብ እንዲደርሱ የጥበቃና እንክብካቤ ሥራዎች በአግባቡ መከናወን እንዲችሉ በከፍተኛና በመለስተኛ የደን ባለሙያዎች አማካይነት ድጋፍ ይደረጋል፡፡

23. ደኖች ተተክለው ከለሙ በኋላ በተለያዩ አካላት የሚቆረጠውን የደን መጠን ማስላትና መተንተን፤ ከፍተኛ የኢኮኖሚ ጠቀሜታ ያላቸውንና ለደን ኢንዱስትሪ ጥቅም የሚውሉ ደንና የደን ውጤቶችን በመለየት የቴክኒክ ድጋፍ መስጠት፤ የተቆረጡ የደን ውጤቶች የዝውውርና የቁጥጥር ፎርማሊቲዎች መሟላታቸውን እና መተካታቸውን ማረጋገጥ፤ በደንና ደን ውጤቶች ዝውውርና ቁጥጥር ላይ ለፍትህ አካላትና ለጉምሩክ ሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት፤ የደን ሰደድ እሳት አደጋ የሚከሰትባቸውን ቦታዎች በመለየት የደን ሀብት በደን እሳት ቃጠሎ እንዳይጠቃ ለመከላከል የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት እና ቅድመ ጥንቃቄዎች በአግባቡ መከናወን እንዲችሉ በከፍተኛና በመለስተኛ የደን ባለሙያዎች አማካይነት ድጋፍ ማደረግ፣ ለህብረተሰቡና በየደረጃው ለሚመለከታችው አስፈጻሚ አካላት ግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠት በደን ሀብት ጥበቃ ዙሪያ የሚከናወኑ ተግባራት ናችው፡፡

24. የደን ሀበቱን የሚመለከቱ መረጃዎችን ማጠናቀር እና የመረጃ ልውውጥ ስራ ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ሲሆን፣ በተለይ የደን ዕሳት አደጋን ለመከላከል የመረጃ

ልውውጥ ስራ ከሀገራዊ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የስራ ሂደት ጋር የሚተገበር ነው፡፡ ለእሳት አደጋ መከላከል ሥራ የሚያስፈልጉ የሎጂስቲክ አቅርቦት በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በኩል የሚመቻች ሲሆን፣ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የመረጃ ልውውጥና የመከላከል ስራውን ግን በተፈጥሮ ሀብት ልማት፤ጥበቃና አጠቃቀም ዋና የሥራ ሂደት ስር በደን እሳት አደጋ መከላከል ባለሙያው አማካይነት ይከናወናል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### የደን ፖሊሲ፣ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያን በተመለከተ

25.የደን ልማት እና ጥበቃ ፖሊሲ፤ስራቴጂና አዋጅን ለማስፈጸም የሚረዱ አግባብነት ያላቸው ደንብና መመሪያዎች ሊወጡ እና ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

26.በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት በናሙና በመለየት መረጃ ከተሰበሰበባቸው ሁሉም አካላት የደን ልማት፣ጥበቃ እና አጠቃቀም ፖሊሲ፤ ስራቴጂና አዋጅን ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብና መመሪያ እንደሌላቸው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እነዚህ የማስፈጸሚያ ደንብና መመሪያዎች አለመዘጋጀታቸው የደን ሀብትን በአግባቡ ለማልማት፣ ለመጠበቅ እና ለመጠቀም የወጡትን አዋጅ፣ ፖሊሲ እና ስራቴጂን ለመተግበር እንዳይቻል አድርጎታል፡፡

27.የሚመለከታቸው የፌደራል ግብርና ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የደን አዋጅ እና ፖሊሲ የወጡት በ1999 ዓ.ም እንደሆነ፤ ወዲያው በማስከተል ማስፈጸሚያ ደንብ እና መመሪያዎች ሊዘጋጁ የሚገባ ቢሆንም መዘግየቱ እንደክፍተት የሚታይ መሆኑን፤ ሆኖም በዚህ በ2004 የሥራ ዘመን መጀመሪያ ላይ የደን ደንብና መመሪያ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለማስፀደቅ ወደ ሚኒስትሮች ምክር ቤት ከስድስት ወራት በፊት የተላከ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኙ አስረድተዋል፡፡

28.ደንን በተመለከተ የወጡ ፖሊሲ፤ ስትራቴጂ እና አዋጅን ለመተግበር የደን ሀብትን በአግባቡ ለማልማት፣ ለመጠበቅ እና ዘላቂነትን በተከተለ ሁኔታ የመጠቀም ልምድን ለማጎልበት ማስፈጸሚያ የሚሆኑ ደንቦችና መመሪያዎች አለመኖር የሀገሪቱን አብዛኛውን የብዝሀ ሕይወት ሀብት የያዙ የተፈጥሮ ደን ሀብቶችን ከፌዴራል ጀምሮ በየደረጃው የሚገኙ ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ ለመጠበቅ እና ለማልማት ሊከናወኑ የሚገባቸው ተግባራትን በአግባቡ ለመተግበር እንዳይቻል አድርጎታል፡፡

## የደን ልማት፣ አጠባበቅ እና አጠቃቀምን የሚመለከቱ ተግባራት በዕቅድ ተካተው የሚተገበሩ መሆኑን በተመለከተ፤

29.የደን ልማት እና ጥበቃ አዋጅ እና ፖሊሲ ላይ የተቀመጡት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተግባር እና ኃላፊነቶች በሚኒስተር መ/ቤቱ ስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ ሊተገበሩ ይገባል፡፡

30.ከ2001 እስከ 2003 ያሉ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዕቅዶች እና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቶች ሲታዩ የደን ልማት፤ ጥበቃና አጠቃቀም ፖሊሲ፤ ስትራቴጂና አዋጅ ላይ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጡ ኃላፊነቶች እና ተግባራት በሚኒስቴር መ/ቤቱ ስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ እንደ አስፈላጊነታቸው እየታዩ በተሟላ ሁኔታ ተካተው እንደማይተገበሩ የተካተቱትም ውስን ተግባራት በዕቅዱ መሰረት ሳይተገበሩ ከዓመት ዓመት እየተንከባለሉ የሚታዩበት ሁኔታ መኖሩን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

31.የደን አዋጅ፣ ፖሊሲና ስትራቴጂ ትግበራ ላይ ከፍተኛ ድክመት እንዳለ በደን ዙሪያ በሚሳተፉ በተለያዩ አካል የሚዘጋጁ የጥናት ጽሁፎች ይገልፃሉ[7]፡፡ ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ ባገኘነው መረጃ መሠረት ደንን በተመለከተ ዕቅድ የሚታቀድ ቢሆንም ተግባራዊ ማድረጉ ላይ የአቅም ውስንነት ስላለ ፖሊሲውን መሠረት ባደረገ ሁኔታ የተፈጥሮ ደን ሀብቱን ለመጠበቅ፣ ለማልማትና ለመጠቀም ባለመቻሉ በዚህ ሀብት ላይ የጎላ ውድመት እየደረሰ መሆኑን፤ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚሁ ክልል በሚገኙ በጉራጌ እና በከፋ ዞን ግብርና ቢሮዎች ደን በተፈጠሮ ሀብት ጥበቃ ስር እንደ ንዑስ ተገባር የተካተተ እንጂ እራሱን ችሎ ስትራቴጂ ዕቅድ እና የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት የማይዘጋጅለት እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በለጠ ጌራ ደን ጽ/ቤት /ሸቤ ሳይት/ ዕቅድ ተይዞለት የሚለማው ሰው ሰራሽ ደኑ ብቻ እንደሆነ እና የተፈጥሮ ደኑ የልማት ዕቅድ ተይዞለት እንደማይሠራ፤ በአጋጣሚዎችም የተሠሩ ሥራዎች ቢኖሩ እንኳ ግልጽ ሆኖ ለመለካት በሚቻልበት ሁኔታ አለመቀመጣቸው ተገልጿል፡፡

[7] በEthiopian Environment Review, FORUM FOR ENVIRONMENT, No, 2010

32.የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ደንን በሚመለከት በሚኒስቴሩ የሚያዙ ዕቅዶች ከዓመት ወደ ዓመት የሚንከባለሉበት ሁኔታ ሊፈጠር የቻለው ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ ድክመት በመኖሩ እንደሆነ፤ ለዚህም እንደ ዋና ምክንያት የሚታየው የሰው ኃይል መልቀቅ በከፍተኛ ደረጃ መኖር እንደሆነ፤ ለወደፊቱ ግን ሁኔታውን በማስተካከል ሰፊ ሥራዎች በማቀድ ለመተግበር ዝግጅት እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

33.ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የተሰጡ ኃላፊነቶች እና ተግባራት እንደ አስፈላጊነታቸው እየታዩ በየደረጃው ስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ ተካተው አለመተግበራቸው፤ የተካተቱትም በዕቅዱ መሠረት ሳይተገበሩ ከዓመት ዓመት እየተንከባለሉ መምጣታቸው የደን ልማት እና ጥበቃ ተግባራት ትኩረት እንዳልተሰጣቸው እና በሀገር አቀፍ ደረጃ የሀገሪቱን የደን ሽፋን ለማሳደግ በየዓመቱ የችግኝ ተከላ የሚከናወን ቢሆንም የተተከለው ችግኝ ለታለመለት ዓላማ እንዲበቃ የሚደረገው ክትትል ላይ የጎላ ድክመት የሚታይ መሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ዋነኛ የመነጋገሪያ አጀንዳ እየሆነ የመጣው የደን ሀብት በአግባቡ እየተጠበቀ እንዳልሆነ ያሳያል፡፡ በእኛ ዕምነት የደን ሀብቱን ከሚደርስበት መጠነ ሰፊ ጥፋት ለመከላከል በሚያስችል መልኩ የማይታቀድበት እና ተግባራዊ የማይሆንት ምክንያት በባለሙያ መልቀቅ ምክንያት ብቻ ሳይሆን ባለው የሰው ኃይል በአግባቡ መሥራት ስላልተቻለ፤ እንዲሁም በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ዘርፍ ለደን ልማት እና ጥበቃ ተግባር እውነታውን ያገናዘበ ትኩረት ስላልተሰጠው ጭምር ነው፡፡

# የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ መዘጋጀትን በተመለከተ፤

34.የሀገሪቱ የመሬት አቀማመጥ እና መሬቱ በደን ቢሸፈን የተሻለ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችልበትን ሁኔታ ያገናዘበ ጥናትን መሠረት ያደረገ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ሊዘጋጅ እና ይህን ዕቅድ መሠረት በማድረግ ለደን ልማት ሊውሉ የሚገባቸው ቦታዎች ተለይተው እንዲታወቁና እንዲያዙ ሊደረግ ይገባል፡፡

35.ስለገጠር መሬት አጠቃቀም የወጣውን አዋጅ መሠረት በማድረግ[8] የአካባቢውን አፈር፣ የመሬት አቀማመጥ፣ የተዳፋትነት መጠን፣ የዕጸዋት ሽፋን፣ የማኅበረሰባዊ

[8] በአዋጅ ቁጥር 456 1997 ክፍል ሶስት ላይ በገጠር መሬት አጠቃቀም ላይ የተጣሉ ገደቦች በሚለው አንቀጽ

ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ ተፋሰስን መሰረት ያደረገ የመሬት አጠቃቀም መሪ ዕቅድ አግባብ ባለው ባለሥልጣን ወጥቶ ተግባራዊ እንደሚሆን የተቀመጠ ቢሆንም ይህ እቅድ ስለመዘጋጀቱ እና ተግባራዊ ስለመሆኑ የሚገልጽ መረጃ ለማግኘት አልተቻለም። በቅርብ እ.አ.አ. በ2009 በተደረገ የምክክር መድርክ ሰነድ ላይ ለእርሻ፣ ለውሀ፣ ለደንና ለሌሎች ሀብቶች ተብሎ ግልፅ በሆነ መልኩ የተከለለ መሬት አለመኖሩ[9]፤ በክልል ደረጃ የመሬት አጠቃቀምን የሚመለከቱ መረጃዎችን በአግባቡ ለማደራጀት የሚያስችል ሥርዓት ለመፍጠር የተደረጉት እንቅስቃሴዎች በጣም ውሱን መሆናቸው እና በክልሎች ሥራውን ሙሉ በሙሉ በባለቤትነት የሚሠራ አካል አለመኖሩን፤እንዲሁም ከኢንቨስትመንት መሬት ጋር በተያያዘ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች በተደራጀ መልኩ ተሰባስበውና ተጠናክረው ለተጠቃሚዎች አለመድረሳቸው ተገልጿል[10]።

36.በደበብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ ለደን ተብሎ ተለይቶ የተመዘገበ ቦታ አለመኖሩን፣ ነገር ግን የተወሰኑ የደን ይዞታዎች በፈር (buffer)፣ ኮር (core) እና ትራንዚሽን (transition) ዞን በሚል መለየታቸውን፤ የመሬት አስተዳደር አዋጅ ቢኖርም ይህን አዋጅ በመጣስ በመንግሥት ጥብቅ ደን ውስጥ ለሰፈሩ ሰፋሪዎች የመሬት የባለቤትነት ደብተር መስጠቱን እና በቴፒ አካባቢ በሚገኝ የተፈጥሮ ደን ውስጥ በመግባትና በመመንጠር ለአንድ ዓመት ያህል እስኪኖሩ ድረስ በቅርብ የሚገኘው የአካባቢው ቀበሌ መስተዳድር አለማወቁን፤ ይህ ደግሞ የተፈጥሮ ደኑን ከመጠበቅ እና ከማልማት አንጻር ከፍተኛ ችግር መሆኑን ከሰበሰብናቸው መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል።

37.የመሬት አቀማመጣቸው በጣም ቁልቁለታማ (45 %) በላይ የሆኑ ቦታዎች ለእርሻ ተግባር እንዳይውሉ በአዋጅ የተቀመጠ ቢሆንም በግልጽ በስፋት እንደሚታየው እና የኦዲት ቡድኑም በአካል ተዘዋውሮ ባያቸው አካባቢዎች ለመመልከት እንደቻለው በደን ሊሸፈኑ የሚገቡ በጣም ቁልቁለታማ የሆኑ ተራሮች ከዓመት ዓመት በመታረስ ላይ መሆናቸውን አረጋግጧል። ይህም ሁኔታ የሀገሪቱ ለም አፈር በከፍተኛ ሁኔታ ለመሸርሸር አደጋ እንዲጋለጥ እያደረገው ይገኛል።

---

9 በNatural resource management and environmental protection: (የኢትዮጵያ የሠላም፣ የልማትና የዲሞክራሲ ሕዝባዊየምክክር መድረክ- ላይ በቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ

10 በኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም እንቅስቃሴና ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በሚል በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ልማትና አጠቃቀም ዳይሬክቶሬት በቀረበው ሪፖርት

38. ለደን ልማት ተግባር ሊውሉ የሚገባቸው ቦታዎቸ ተለይተው ሊያዙ ባለመቻላቸው እንዲሁም ያለውም የመሬት አጠቃቀም ፖለሲ አተገባበር ላይ ድክመት ስለሚታይ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ተቀናጅቶና ተወያይቶ ለደን፣ ለእርሻ፣ ለኢንቨስትመንት ወዘተ የሚውል መሬት በአግባቡ ተከልሎ ባለመለየቱ በተለይ የተፈጥሮ ደኑ በህገወጥ ሰፈራ፣ የአካባቢ ተጽዕኖ ባልተጠናባቸው የልማት ሥራዎች በከፍተኛ ሁኔታ ጉዳት እየደረሰበት ይገኛል።

# የጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ልማት፣ አጠባበቅና አጠቃቀምን በተመለከተ

## የጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ልማትን በተመለከተ፤

39. በነባር የተፈጥሮ ደን ሀብትነት የተያዙት ይዞታዎች ውስጥ የብዝሀ ሕይወት ስብጥርም ሆነ የይዞታ መጠን እንዲጨምር በጥናት ላይ የተመሠረተ የሀገር በቀል የዛፍ ችግኝ ተከላ እንዲከናወን እንዲሁም በመንግስት ጥበቃ ይደረግላቸዋል ከተባሉት ደኖች በተጨማሪ ተመሳሳይ ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገቡ የተፈጥሮ ደኖች በጥናት እንዲለዩ በማድረግ አቅምን ባገናዘበ መልኩ የIUCN (አባሪ 7)[11] የተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ደረጃን መሠረተ ባደረገ ሁኔታ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ሊደረግ ይገባል።

40. በጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታነት ቀደም ብለው የተያዙት ይዞታዎች በጥናት ላይ ተመሠረተ ሁኔታ የብዝሀ ሕይወት ስብጥራቸው መጠን እንዲጠበቅ ብሎም እንዲጨምር የሀገር በቀል የዛፍ ችግኝ ተከላ ስለመከናወኑም ሆነ የይዞታቸው ስፋት መጠን እንዲጠምር የተደረገ ጥረት ስለመኖሩ እንዲሁም በነባር የተፈጥሮ ደን ሀብትነት ከተያዙት እና በመንግስት ጥበቃ እየተደረገላቸው ካሉት በተጨማሪ ተመሳሳይ ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገቡ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች በጥናት ተለይተው እንዲያዙ ስለመደረጉ መረጃ ማግኘት አልተቻለም። ይህንኑ በተመለከተ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው መጠይቅ በሰጡት መልስ አሁን ባለው ሁኔታ በነባር የተፈጥሮ ደን ሀብትነት ከተያዙት እና

---

[11] Defining Protected Areas: *IUCN Protected Areas Categories Summit—Almeria, Spain—May 2007;* Forests and Protected Areas: *Guidance on the use of the IUCN Protected area management categories*

በመንግስት ጥበቃ እየተደረገላቸው ካሉት በተጨማሪ በዚህ መልክ የተያዙ አዳዲስ የተፈጥሮ ደኖች በትግራይ፣ በአማራ እና በኦሮሚያ አንዳንድ አካባቢዎች የተለዩ አካባቢዎች ስለመኖራቸው ገልፀዋል፡፡

41. በነባር የተፈጥሮ ደን ሀብትነት ከተያዙት እና በመንግስት ጥበቃ እየተደረገላቸው ካሉት በተጨማሪ ተመሳሳይ ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገቡ የተፈጥሮ ደኖች በጥናት እንዲለዩ በማድረግ አቅምን ባገናዘበ መልኩ የIUCN (አባሪ 7) የተፈጥሮ አካባቢ ጥበቃ ደረጃን መሠረተ ባደረገ ሁኔታ ጥበቃ እንዲደረግላቸው ካልተደረገ የሀገራችን የብዝሀ ሕይወት ሀብት በአብዛኛው የሚገኘው በእንዚህ የተፈጥሮ ደኖች እንደመሆኑ መጠን ለተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ የመድሀኒትነት ጠቀሜታ ያላቸው፣ እንዲሁም ለወደፊቱ ሊኖራቸው የሚችለው ገና ያልተጠኑ በቀላሉ ሊገመቱ የማይችሉ የብዝሀ ሕይወት ሀብቶች ሊጠፉ የሚችሉበት ሁኔታ ይከሰታል፡፡ በጠቅላላ ሀገራችን ከደን ሀብቷ ልታገኘው የምትችለውን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ሌሎች ጠቀሜታዎች በሚፈለገው መጠን ለማግኘት የሚደረገውን ጥረት ፈታኝ ያደርገዋል፡፡

## የጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ጥበቃ እና ቀጣይነት ያለው አጠቃቀምን በተመለከተ፤

### *ቅድሚያ የተሰጣቸው  የሀገሪቱ ጥብቅ የተፈጥሮ ደኖች አስተዳደርን በተመለከተ፤*

42. ቅድሚያ ለተሰጣቸው የሀገሪቱ ጥብቅ የተፈጥሮ ደኖች የአስተዳደር ፕላን (Site Mamagement Plan) እንዲዘጋጅላቸው፣ ዳርድንበራቸው ተከልሎና ተመዝግቦ በሕግ መሠረት ዕውቅና እንዲያገኙ፣ እንደአስፈላጊነቱ በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥታት እንዲተዳደሩ፣ በየጊዜው የያዙት የመሬት ሽፋን እንደ አካባቢው ሁኔታው እየታየ እንዲያድግ እና የያዙት የብዝሀ ሕይወት ስብጥርና መጠን ላይ ጥናት በማድረግ በጥናቱ ውጤት መሠረት ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

43. በመስክ በናሙና በመለየት ያየናቸው ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶችን በሚመለከት ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመገንዘብ የተቻለው ቅድሚያ የተሰጣቸው የሀገሪቱ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች አብዛኛዎቹ የአስተዳደር ፕላን (Site Mamagement Plan) ያልተሠራላቸው መሆኑን፣ ጥቂት የተሠራላቸው ቢኖሩም የቆየ እና ወቅታዊነት የሚጎለው መሆኑን እና ዳር ድንበራቸው ተከልሎና ተመዝግቦ በሕግ መሠረት ዕውቅና እንዲያገኙ ያልተደረገ መሆኑን ነው፡፡

44. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ከሚገኙ 10 ቅድሚያ የተሰጣቸው የመንግስት ደኖች መካከል ለስምንት ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች የማናጅመንት ፕላን (Site Mamagement Plan) አለመሠራቱ፣ ዳር ድንበራቸው ተከልሎና ተመዝግቦ በሕግ መሠረት ዕውቅና እንዲያገኙ አለመደረጉ እና የብዝሀ ሕይወት ስብጥር መጠናቸው ላይ ጥናት አለመደረጉን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአካል የጎበኘናቸው 8 ጥብቅ የመንግስት የተፈጥሮ ደኖች ይዞታ ላይም ተመሳሳይ ሁኔታ እንደሚታይ እና ቅድሚያ ከተሰጣቸው የመንግስት ደኖች መካከል በናሙና የታዩት እነዚህ የመንግስት ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች የደን ይዞታ አስተዳደር ኘላን የሌላቸው ከመሆኑም በላይ በመናገሻ ሱባ እና ጭልሞ ጋጂ ቅድሚያ የተሰጣቸው የመንግስት ደኖች በየጊዜው ከአካባቢው ኅብረተሰብ በሚደርሰው ጫና የነበረውን የደን ክልል የሚያመለክት ምልክትን በማለፍ በደኑ ይዞታ ውስጥ መኖሪያዎች የተሠሩ መሆናቸውን እና የደኑ የቀድሞ ይዞታን የሚያሳየው ዳር ድንበር አለመከበሩን፤ ይህ ደን ቀደም ሲል የደን አስተዳደር ኘላን የነበረው ቢሆንም በአግባቡ አለመተግበሩን እና እንደገና ታይቶ ካለው ወቅታዊ ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ እንዲሻሻል አለመደረጉን ከሰበሰብናቸው መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል (ፎቶ1 እና 2)፡፡

45. የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ይህን ተገባር በቀጥታ የማከናወን ኃላፊነት የክልሎች መሆኑን እና ካላቸው አቅምና በጀት አነስተኛነት አንፃር የደን አስተዳደር ኘላን (Site Mamagement Plan) አጠናቆ ለመሥራት ጊዜ የሚወስድ እንደሆነ፤ አሁን የተፈጥሮ ደን ሀብቱን ለመጠበቅ እንደ ስልት ተግባራዊ እየሆነ ያለው አሳታፊ የደን አስተዳደር (partisipatory forest management) መሆኑን እና በቅርብ ዓመታት መተግበር የጀመረ በመሆኑ ለተፈጥሮ ደን ይዞታዎች ማኔጀመንት ኘላን የማዘጋጀትም ሆነ ድንበራቸውን የመከለል ተግባር የሚከናወነው የአካባቢው ሕብረተሰብን በማሳተፍ እና በመግባባት በመሆኑ ጊዜ እንደሚጠይቅ ገልፀዋል፡፡

46. የመንግስት ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች የደን ይዞታ ማረጋገጫ እና አስተዳደር ኘላን እንዲኖራቸው አለመደረጉ ከአካባቢው ኅብረተሰብ በሚደርሰው ጫና ይዞታቸው ከጊዜ ወደጊዜ እየቀነሰ እንዲመጣ ያደረገው ሲሆን፣ የቆየ ቢሆንም ቀደም ሲል የደን አስተዳደር ኘላን (management plan) የነበራቸው ቢሆኑም በአግባቡ ባለመተግበሩ

እና ካለው ወቅታዊ ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ እንዲሻሻል ባለመደረጉ የተፈጥሮ ደን ሀብቱን ይዞት በሚጠበቀው ደረጃ ለመጠበቅ አላስቻለም።

### ለጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች ተገቢው ጥበቃ የሚደረግላቸው መሆኑን በተመለከተ፤

47. በመንግስት ይዞታ ስር ለሚገኙ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ከአካባቢው ሕብረተሰብ በሚቀጠሩ የደን ዘቦች ጥበቃ ሊደረግላቸው፤ ከህገ ወጥ ሠፋራ፣ ከደን ጭፍጨፋ እና ከሌሎች ደኑን ከሚጎዱ ሁኔታዎች እንዲጠበቁ በማድረግ ለተፈለገው ጥቅም እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል።

48. በናሙና በታዩት በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች እና በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስታት ስር በሚተዳደሩት ቅድሚያ የተሰጣቸው ጥብቅ የተፈጥሮ ደኖች /ቡታጅራ/ ተገቢው ጥበቃ እንደማይደረግላቸው ፤ ለተወሰኑት ማለትም ለቦንጋ፣ በለጠጌራ፣ ባቢያ ፎላ፣ መናገሻ ሱባ እና ጪሊሞ ጋጂ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን አካባቢዎች ከስፋታቸው አንፃር ለማዳረስ ስለማይቻል ቁልፍ በሆኑ ቦታዎች ብቻ ጥበቃ የሚደረግላቸው መሆኑን፤ በተጨማሪም ፓርኮችን ጨምሮ ቅድሚያ የተሰጣቸው ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ቦታዎች በቂ ትኩረት እንዳልተሰጣቸው እና እየተመነጠሩ ወደ ሌላ አገልግሎት እየተለወጡ እንደሚገኙ፣ በደኑ ላይ ጥፋት ሲደርስ ሁኔታውን ወደ ህግ ለማቅረብ ጥረት ሲደረግ በህግ አካላት በኩል አፋጣኝ እና ተመጣጣኝ ቅጣት የመጣሉ ሁኔታ ከጊዜ ወደ እየተዳከመ መሆኑን፤ በጥበቃ ሠራተኞች እና በደን ባለሙያዎች ንብረት እና አካል ላይ ጉዳት ማድረስ ብሎም እስከ ሕይወት ማጥፋት ጥቃት እየደረሰ እንደሚገኝ እና ተያያዥ የሆኑ አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንደሚታዩ በቦታው በመዘዋወር ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመገብዘብ ተችሏል።

49. በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ ጥብቅ የተፈጥሮ ደኖች /በለጠጌራ፣ባቢያፎላ፣ሲግሞ ሰጠማ፣ጢሮ ቦተር በቾ፣ ጭላሎ ጋለማ፣ በሻሸመኔ ሙኒሳ በአርሲ ነገሌ አካባቢ አዳባ ዶዶላ፣መናገሻ ሱባ፣ ጪሊሞ ጋጂ /ላይ ህገወጥ ሰፈራ፣ ደን ጭፍጨፋ እና ሌሎች ደኑን የሚጎዱ ነገሮች የሚደርስባቸው መሆኑን እና በአግባቡ ከጉዳት እንዳልተጠበቁ (ፎቶ 2,3) እና ወደ ደኑ እሳት የመልቀቅ፣ በህገ ወጥ ጣውላ ምርት እና በጥናት ላይ ባልተመሠረተና መናበብ በለሌበት ሁኔታ በሚተገበሩ ልማቶች በደኑ ላይ ተፅኖ እያሳደሩ ባመሆናቸውን፤ በእነዚህ ጥብቅ የመንግስት የተፈጥሮ ደን

ውስጥ የሰፈሩትን ህገወጥ ሰፋሪዎች ለማስወጣት ክስ ቢመሰረትም ወረዳም ሆነ ሌሎች የሚመለከታቸው አካለት መልስ ሊሰጡበት አለመቻላቸው እና የሚሰጠው የህግ ከለላ ደካማ መሆኑን በመስክ ከሰበሰብናቸው መረጃዎች ለመገንዘብ ችለናል ፡፡

ፎቶ2፤በሻሸመኔ ሙኒሳ በአርሲ ነገሌ አከባቢ የሚገኝ ቅድሚያ የተሰጠው ጥብቅ የመንግስት ደን ውስጥ በህገወጥ መልኩ ተመንጥሮ ወደ እርሻ መሬትነት የተለወጠ / መጋቢት 2004 ዓ/ም/

ፎቶ3፤ በጭላሎ ገለማ ቅድሚያ የተሰጠው የመንግስት ደን በህገወጥ መልኩ ተመንጥሮ የእርሻ መሬትና የገበሬዎች መንደር ከመሆኑ ባሻገር ከጫፍ እስከ ጫፍ ደኑ በእሳት ሲቃጠል የነበረው ከፍተኛ ጪስ /መጋቢት 2004 ዓ/ም/

50. ቅድሚያ በተሰጣቸው ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች ውስጥ ከጅማ ወደ ሚዛን ለሚገነባው መንገድ ግብአት የሚሆን ድንጋይ እና ጠጠር ለማምረት በደኑ መሀል በመግባት /በቦንጋ ልዩ ቦታው 466 በመባል የሚታወቅ እና በበለጠጌራ/ ዕድሜ ጠገብ እና በቀላሉ ሊተኩ የማይችሉ የሀገሪቷ የተፈጥሮ ደኞች በከፍተኛ ደረጃ እየወደሙ እንደሚገኙ፤ችግሩ በዚህ የሚያቆም አለመሆኑና ድንጋይ እና ጠጠር ለማውጣት በተደረገው ቁፋሮ የተፈጠሩ ትላልቅ ጥልቀት ያላቸው ገደሎች በሚዘንበው ዝናብ መሬቱ እየተደረመሰ ከላይ ተሸክሟቸው የነበሩ ትላልቅ ሀገር በቀል ዛፎች ወደ ገደሉ ገብተው ጥቅም ሳይሰጡ በመበስበስ ቀጣይነት ያለው ጉዳት ሊያደርስ የሚችልበት ሁኔታ የሰፋ መሆኑን የኦዲት ቡድኑ በአካል ለማየት ችሏል (ፎቶ 4)፡፡



ፎቶ 4፤ የቦንጋ ቅድሚያ የተሰጠው ጥብቅ የመንግስት ደን 466 በመባል የሚታወቅ ቦታ ላይ ከጅማ ሚዛን ለሚሰራው መንገድ የድንጋይና ጠጠር መውጫ በመደረጉ የደረሰው ከፍተኛ ጉዳት የሚያሳይ ፎቶግራፍ፡፡ /የካቲት 2004 ዓ/ም/

51.በለጠ ጌራ ደን ጽ/ቤት /ሸቤሳይት/ ስር የሚተዳደሩ ቅደሚያ የተሰጣቸው የመንግስት ደኖች ለመጠበቅ ጥረት ቢደረግም በህገወጥ መንገድ የደን ይዞታው ለግለሰቦች የሚመራበት ሁኔታ መታየቱን፤ የደኑን ድንበር በማለፍና በመግባት የቡና ተክላ እየተከናወነ መሆኑን፤ በዚህ ምክንያት የደኑ ብዝሀ ህይወት ሀብት በከፍተኛ ደረጃ እየተመናመነ እንደሚገኝ እና በጌራ አካባቢ የደኑ ይዞታ ለባላሀብት ተሰጥቶ ወደ ሰባት ሄክታር ከተመነጠረ በኋላ በዞኑ ደን ጽ/ቤት ጥረት ለመግታት መቻሉን፤ ያልተጠና ኢንቨስትመንት ደኑን በጣም እየጎዳው መሆኑ፤ ለቡና ባለ ሀብቶች ደኑ ውስጥ መሬት እንደሚሰጥና ደኑ በጣም እየተጎዳ እንደሆነ የጽ/ቤቱ የደን ባለሙያ ገልፀዋል፡፡



ፎቶ 5፤ የበለጠ ጌራ ቅድሚያ የተሰጠው የመንግስት ደን በህገወጦች ተጨፍጭፎ ተጭኖ ሊወሰድ ሲል ለፖሊስና ለሸቤ የደን ጽ/ቤት ጥቆማ በመድረሱ በቁጥጥር የዋለ የግንድ ቁራጮች የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ፡፡ /የካቲት 2004 /

52. የሀገሪቷ የተፈጥሮ ደን በእርሻ መስፋፋት ምክንያት እየወደመ እንደሆነ በኦሮምያ፣ በደቡብ እና በጋምቤላ ክልሎች በየዓመቱ 59000 ሄክታር የተፈጥሮ ደን የሚወድም መሆኑ እንደሚገመትና በሌሎች ክልሎችም ተመሳሳይ እንደሆነ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጁ የጽሁፍ ሰነዶቸ የሚገልጹ ሲሆን[12]፣ የተለያዩ ወረዳዎችን የሚያካልሉ ጥብቅ የተፈጥሮ ደኖች ይዞታ /ቦንጋ/ በቀበሌ መስተዳድር አካላት ለግለሰቦች ለእርሻ መሬት እየተሰጡ መሆናቸውን፤ በክልል እና በወረዳ ካለበቂ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ለባለሀብት ለልማት በሚል የሚሰጡበት ሁኔታ እንዳለ፤ የተወሰኑት ፍ/ቤት ቀርበው እንዲቀጡ ቢደረግም የደን ምንጠራው እና ህገወጥ ሰፈራው አሁንም የቀጠለ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

53. የአካባቢውን ኅብረተሰብ ባሳተፈ ሁኔታ (participatory forest management-PFM) ቅድሚያ የተሰጠው የመንግስት ደን /ቦንጋ፣አዳባ ዶዶላ፣ በለጠ ጌራ፣ ጨሊሞ ጋጂ/ መጠበቅ እንደሚሻል አማራጭ በማየት መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች (Farm Africa-SOS sahl, GIZ, JICA) ድጋፍ ጥበቃ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ እና በተወሰነ ደረጃ የተሻለ ውጤት የታየ ቢሆንም ደኑን ዘላቂ በሆነ ሁኔታ ለመጠበቅ ውል ገብተው የሚንቀሳቀሱት የማኅበረሰብ ክፍሎች ውሉን በመጣስ የጥላ ዘፎችን ብቻ በመተው ደኑን በመመንጠር የቡና ተከላ የሚያከናውኑበት ሁኔታ እንዳለ ከተሰበሰቡ መረጃዎቸ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

54. የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የኢንቨስትመንት ሁኔታ በተለይ በመጀመሪያ አካባቢ በአካባቢው ሊያመጣ የሚችለው ተጽዕኖ ሳይገመገም የሚሰጥበት ሁኔታ እንደነበረ፣ ሠፈራን በተመለከተ በመንግስት የሚከናወኑ ሥፈራዎች ጥቅጥቅ ያለ ደን በሌለበት እንዲከናወኑ፤ በአጠቃላይ የደን ፖሊሲውን ለመተግበርና ደንን ከጭፍጨፋና ከሌሎች ጎጂ ነገሮች ለመጠበቅ ካለው የአቅም ማነስ በተጨማሪ አግባብነት ያላቸው ደንብና መመሪያዎችን በወቅቱ አዘጋጅቶ ተግባራዊ በማድረጉ ረገድ መዘግየት መታየቱ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊነት ወስዶ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር የማድረግ ሥራ አለመስራቱን ገልጸዋል፡፡

---

[12] የኢትዮጵያየተፈጥሮሃብትልማት፣ጥበቃናአጠቃቀምእንቅስቃሴናትኩረትየሚሹጉዳዮች ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ልማትና አጠቃቀም ዳይሬክቶሬት Report to Public consultation forum of Ethiopia on peace, development and democracy December 23, 2009

55. ለእነዚህ ውስን ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ድንበራቸው ተከልሎ ሕጋዊ እውቅና ያለው ይዞታ እንዲኖራቸው አለመደረጉ እና የደን አስተዳደር ኘላን (Site Mamagement Plan) አለመሠራቱ፤እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት ድጋፍ የሚያከናወነው ኀብረተሰብን ያሳተፈ የደን ሀብት ጥበቃ ተግባር ዘላቂነት ባለው ሁኔታ የተፈጥሮ ደን ሀብቱን ለመጠበቅ እንዲችል በመንግስታዊ ባለድርሻ አካላት በኩል የሚደረገው ዝግጁነት እና ድጋፍ አጥጋቢ አለመሆኑ፤ በእነዚህ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች ላይ በተለያዩ አካላት ለሚደርሱ ጥፋቶች በፍትህ አካላት በኩልም ተገቢውን ህጋዊ ድጋፍና ውሳኔ ማግኘት ባልተቻለበት ሁኔታ ያለበቂ የህግ ከለላ መጠነ ሰፊ ጥፋት እየደረሰባቸው በመሆኑ የተፈጥሮ ደን ሀብቱን በተሻለ ሁኔታ በማልማት የተሻለ ጠቀሜታ እንዲሰጡ ለማድረግ አላስቻለም፡፡ በእኛ አስተያየት በተፈጥሮ ደን ሀብቱ ላይ እየደረሰ ካለው መጠነ ሰፊ ጉዳት አንፃር ሳይንሳዊ ጥናት ገና ያልተደረገባቸው፤ ከወደሙ በኂላ ምንም አይነት ጥረት ቢደረግ ለመተካት የማይቻለውን የሀገሪቱን የብዝሀ ህይወት ሀብት የያዙ በጣም ውስን ቦታዎችን ሀገሪቱ  በአጭር የምታጣበት ሁኔታ ሊከሰት ስለሚችል ሁሉም ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መንገድ አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

## ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎችን ከድንገተኛ እሳት ቃጠሎ መከላከልን በተመለከተ፤

56. ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎችን ከድንገተኛ እሳት ቃጠሎ ለመከላከል በተፈጥሮ ባህሪያቸው የደን እሳት መከላከል የሚችሉ የዕጽዋት አይነቶች በጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ይዞታ ዙሪያ በሁለትና በሶስት ረድፍ ሊተከሉ፤ የመንግሥት ደኖችን ከእሳት አደጋ ለመከላከል የሚያስተባብር እና ድጋፍ የሚያደርግ የደን እሳት መከላከያ ብርጌድ በየደረጃው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ተውጣጥቶ ሊቋቋም ይገባል፡፡

57. በመስክ ናሙና በመለየት ባየናቸው ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች ዙሪያ በባህሪያቸው እሳት መከላከል የሚችሉ የዛፍ ዝርያዎች እንዲተከሉ አልተደረገም፡፡ ባለፉት 16 ዓመታት /እ.ኤ.አ ከ1992-2008/ በዝቋላ ተራራ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታን ጨምሮ በየዓመቱ የደን ቃጠሎ እየተከሰተ በአጠቃላይ 25000 ሄክታር ደን በእሳት መውደሙን፤ ጥብቅ የተፈጥሮ ደኖችን ከሚያስተዳድሩ አካላት ባገኘነው መረጃ መሠረት የመንግስት ደኖች ከእሳት ቃጠሎ ለመከላከል የሚያስችል

በየደረጃው ከሚመለከታቸው አካላት የተውጣጣ የደን እሳት መከላከያ ብርጌድ እንዳልተቋቋመ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

58. የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ አሁን እየተከተሉት ያለው የደን አስተዳደር ዓይነት አሳታፊ የደን አስተዳደር እንደሆነ እና መተግበር ከጀመረ ጥቂት ዓመታት ማስቆጠሩን፤ በዚህ አስተዳደር መሠረት ቅድሚያ የተሰጣቸው የመንግስት ደኖች በተፈጥሮ ባህሪያቸው የደን እሳት መከላከል የሚችሉ ዕፅዋት ዓይነቶች ጥናት በማድረግ በሁለት እና በሦስት ረድፍ በዙሪያቸው እንዲተከሉ ማድረግ የሚቻለው ከአካባቢው ሕብረተሰብ ጋር በመተባበርና በመግባባት በመሆኑ ጊዜ እንደሚጠይቅ፤ በተጨማሪም ይህን በቀጥታ የሚያከናውኑት ክልሎች ስለሆኑ ካላቸው የሰው ዓቅምና በጀት አንፃር ፍጥነቱ ወሱን መሆኑን ገልፀዋል፡፡

59. ይህ የተገለጸው የአቅም ውስንነት ቶሎ የሚቀረፍበት ሁኔታ ካልተመቻቸ የደን እሳትን በመከላከሉ ረገድ ብቻ ሳይሆን በአጠቃላይ የሀገሪቱን የደን ሀብት በአግባቡ ለማልማት እና ሊያበረክት የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲሰጥ ለማድረግ አያስችልም፡፡ በተፈጥሮ ባህሪያቸው የደን እሳት መከላከል የሚችሉ ዕፅዋት ዓይነቶች ጥናት በማድረግ በሁለት እና በሦስት ረድፍ በዙሪያቸው እንዲተከሉ ባለመደረጉ ከገበሬዎች ማሳ ወይም ከሌላ ቦታ የሚነሳ እሳት በደኑ ውስጥ በመግባት በቀላሉ ጉዳት እያደረሰ ሲሆን፣ በደን ላይ የሚነሳ እሳት ከአንዱ የደን ክልል ወደ ሌላው የደን ክልል በቀላሉ በመዛመት ተያያዥነት ያላቸው ደኖች በከፍተኛ ሁኔታ በእሳት እንዲጠፉ ያደርጋቸዋል፡፡ በየደረጃው ከሚመለከታቸው አካላት የተውጣጣ የደን እሳት መከላከያ ብርጌድ እንዲቋቋም ባለመደረጉ በተለያዩ ግዚያት በደን ላይ የሚነሱ የእሳት ቃጠሎዎች ለማጥፋት ህብረተሰቡን አነሳስቶና አደራጅቶ እሳቱ እንዲጠፋ ለማድረግ ግዜ ስለሚወስድና የሚፈለገውን ኃይልም ለማግኘት አዳጋች የሚሆንበት አጋጣሚዎች ስላሉ በደን ውስጥ የተነሱ የእሳት ቃጠሎዎች በቀላሉ ስለማይጠፋ ሰፊ ሽፋን ያለው ደን እንዲወድም ምክንት ሆንዋል፡፡



ፎቶ 6፤ ሚንቾ በሚባል አካባቢ በጢሮ አበልቴ ቅድሚያ የተሰጠው የመንግስት ደን የደረሰው የእሳት ቃጠሎ የሚያሳይ ፎቶግራፍ። /የካቲት 2004 ዓ/ም

## *የደን ሀብት መቆጠጠሪያ ኬላ ማቋቋምን በተመለከተ፤*

60.በመንግሥት ደኖች መግቢያና መውጫ መንገዶች ላይ የደን ሀብት መቆጠጠሪያ ኬላ ሊቋቋም እና በደን ሀብቱ ላይ የሚደርሰውን ህገወጥ ጭፍጨፋ ለመቆጣጠር ጥረት ሊደረግ ይገባል።

61.በናሙና በመለየት የተመለከትናቸው ሁለት ክልሎች ስር እየተዳደሩ ያሉት ቅድሚያ የተሰጣቸው የመንግስት ደኖች መግቢያና መውጫ መንገዶች ላይ የደን ሀብት መቆጣጠርያ ኬላ እንዲቋቋም አልተደረገም።

62.ለሚመለከታቸው የፌደራል ግብርና ሚ/ር የሥራ ኃላፊዎች ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ በአጠቃላይ በአገሪቱ በኬላ ማቋቋምና በጥበቃ ዙሪያ ወጥ የሆነ አቋምና አመለካከት አለመኖሩን፤ አንዳንድ ክልሎች ሕብረተሰቡን በማሳተፍና በማሳመን መከላከል እንችላለን የሚል እምነት ሲኖራቸው፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ከዚህ በተጨማሪ የኬላ መቋቋም እንደ ወሳኝ ተግባር የሚመለከቱ መሆኑን፤ ይህን ጉዳይ በተመለከተ አንድ ወጥ የታመነበት አቋም አለመኖሩን በቀጣይ ምክክር እና ግልጽ አቋም እንዲኖር ጥረት የሚጠይቅ ክፍተት እንደሆነ ገልፀዋል።

63.በመንግሥት ደኖች መግቢያና መውጫ መንገዶች ላይ የደን ሀብት መቆጠጠሪያ ኬላ እንዲቋቋም ባለመደረጉ የተፈጥሮ ደን ሀብቱ ካለምንም ሥጋት በስፋት በህገወጥ መልኩ እንዲጨፈጨፍ እና እንዲገዝዝ አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል።

## ለልማት ተግባር የሚሰጡ ቦታዎች በተፈጥሮ ደን ሀብቱ ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩ ማድረግን በተመለከተ፤

64. ለልማት ተግባራት የሚፈቀዱ ቦታዎች በሀገሪቱ የተፈጥሮ ደን ሀብት ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩ ለማድረግ እንዲቻል ለልማት ተግባር የሚሆኑ ቦታዎች በቅድሚያ ተጠንተው እንዲለዩ ሊደረግ ይገባል፡፡

65. በተለያዩ ክልሎች ከግብርና ኢንቨስትመንት ጋር በተያያዘ ወደ 5200 ባለሀብቶች ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ ቦታ የወሰዱ ቢሆንም ከዚህ ውስጥ በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል የተሰጠው ለ30 ብቻ በመሆኑ እና ቀሪው 5170 በክልሎች የተሰጠ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በክልል ከተሰጡት ቦታዎች ውስጥ ለ5105 ባለሀብቶች 2.1 ሚሊየን ሄክታር መሬት የአካባቢ እና የማኀበረሰብ ተጽዕኖ ሳይጠና የተሰጠ ሲሆን፣ ለ95 ባለሀብቶች ግን የአካባቢ እና የማህበረሰብ ጥናት መጠናቱና አለመጠናቱን ለማወቅ የተቻለ ቢሆንም ምን ያህል ሄክታር መሬት እንደተሰጠ ለማረጋገጥ መረጃ ለማግኘት አልተቻለም (አባሪ 4.1)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሸካ ዞን ብቻ እ.አ.አ እስከ 2006 ድረስ 9,951 ሄክታር የተፈጥሮ ደን ይዞታ በተመሳሳይ ለባለሃብቶች የተሰጠ እና እየተሰጠ ያለበት ሁኔታ በዞኑ በተደረገ ጥናት ተገልጿል (አባሪ 5.1)[13]፡፡

66. የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ማከናወንና ተገቢውን ክትትል ማድረጉ ልማቱ ቀጣይነት እንዲኖረው ለማድረግ ከሚያበረክተው አስተዋጽኦ በተቃራኒ የልማት ተግባራት እንዳይከናወን እንደ እንቅፋት የማየት የተሳሳተ ግንዛቤ እንዳለ፤ በዚህ የአካባቢ ተጽዕኖ ጥናት ላይ በዳይሬክተሩ ያለው የሰው ኃይል እስከ ቅርብ ጊዜ ማለት እስከ 2004 ሶስተኛ ሩብ ዓመት ድረስ አንድ ሰው ብቻ እንደነበረ እና በቅርብ ሶስት ተጨማሪ የሰው ኃይል ለመቅጠር በሂደት ላይ እንደሆነ፤ በክልሎች የተሰጠው መሬት በምን ደረጃ ላይ እንዳለ ክትትል ተደርጎ መረጃው በተሟላ መልክ የተያዘበት ሁኔታ እንደሌለ  ከግብርና ኢንቨስትመንት ድጋፍ ዳሬክቶሬት ዳይሬክተር ገለጻ ለማወቅ ተችሏል፡፡

67. በጅማ ዞን ደንና ዱር እንስሳት ጥበቃ ጽ/ቤት ስር የሚገኙ በለጠ ጌራ፣ ባቢያ ፎላ፣ ሲግሞ ሰጠማ እና ቦቸ የተባሉ ጥብቅ የተፈጥሮ ደኖች በጥናት ላይ ባልተመሰረተና

---

[13] Forests of Sheka: Ecological, social, legal and economic dimensions of recent anduse/ landcover changes—overview and synthesis, *Tadesse Woldemariam* and *Masresha Fetene*

መናበብ በለሌበት ሁኔታ በሚተገበሩ ልማቶች አሉታዊ ተፅዕኖ እየደረሰባቸው እንደሚገኝ የጽ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

68. ለሚመለከታቸው የግብርና ሚ/ር የሥራ ኃላፊዎች ሁኔታውን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ በአገር ደረጃ የጸደቀ የመሬት አጠቃቀም ኘላን (Land use plan) ባለመኖሩ ደኖች መመንጠር አለባቸው የሚል አሠራር አለመኖሩን በመጥቀስ መሬትን እንዴት መጠቀም እንደሚገባ በገጠር ልማት ፖሊሲ እና እስትራቴጂ ላይ በግልጽ የተቀመጠ በዚሁ ማዕቀፍ ውስጥ የሚታይ መሆኑን፤ ሆኖም ዋናው ችግር ወደመሬት ወርዶ ተግባራዊ አለመደረጉ እንደሆነ እና ተግባራዊ ለማድረግም ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ እና እስካሁን በድፍረት ያልተገባበት መሆኑን፤ በአሁኑ ወቅት ግን ሁኔታውን ለመንግስት በማቅረብ ተግባራዊ ለማድረግ እንቅስቃሴ መጀመሩን፣ የደን ጉዳይም በዚሁ መፍትሄ እንደሚያገኝ ገልጸዋል፡፡

69. በተፈጥሮ ደን ሀብት አጠባበቅ ዙሪያ በተለያዩ አካላት የተዘጋጁ ጥናታዊ ጽሁፎች እ.ኤ.አ በ2008 በሻኪሶ፣ አዶላ፣ ቦሬ እና በተለያዩ የኦሮምያ ወረዳዎች 5268 ሄክታር፣ ሶራ በተባለ ቦታ 12700 ሄክታር፤ በባሌ ዞን ዘጠኝ ወረዳዎች 12825 ሄክታር፤ ለጋ ጃርቲ በተባለ ቦታ መጠኑ ያልታወቀ የተፈጥሮ ደን መቃጠሉን ይገልፃሉ፡፡ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚገኙ /ከነቀምት ወደ በደሌ ሲኬድ ዴዴሣ አካባቢ፣ በመተማ ወዘተ…/ የተፈጥሮ ደን ሀብቱ ሊሰጥ ከሚችለው አካባቢያዊ ጠቀሜታ ጋር ሳይገናዘብ እና የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ ሳይከናወን ለልማት ውሏል በሚል ሀሳብ ብቻ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ለውድመት እየተጋለጡ መሆኑን፤ በአማራና እና በትግራይ ክልሎች ሠፈራ በተከናወነባቸው ቦታዎች የተፈቀደላቸውን የይዞታ መጠን በማለፍ ሊጠቀሙ ከሚችሉት በላይ የአካባቢውን የተፈጥሮ ደን በመቁረጥ እና በማቃጠል የጎላ ጥፋት እያደረሱ መሆኑን[14] ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በየዓመቱ 141 ሺህ ሔክታር የሀገሪቱ የደን ሀብት የሚወድም እንደሆነ በጥናቶቹ ተገልጿል[15],[16]፡፡

70. ከዚህም በተጨማሪ ጉራፈርዳ፣ ሸኮ መዠንገር እና የኪ አካባቢዎች ትልልቅ ሀገር በቀል ዛፎችን የያዙ የተፈጥሮ ደኖች እየተመነጠሩ ለእርሻ ቦታ ማስፋፊያ እና ለሌሎች የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ በአግባቡ ላልተጠናላቸው የልማት ሥራዎች እየዋሉ መሆናቸውን፣ ይህንኑ ተከትሎ የአካባቢው ኅብረተሰብ ጠብቆ ያቆየው ደን ኅብረተሰቡን ባላሳተፈ እና በማያውቀው ሁኔታ ለባለ ሀብት ተሰጥቶ የሚወድም ከሆነ በሚል ስሜት ህብረተሰቡ ደኑን መመንጠር መጀመሩን፤ ቡና እናለማለን

---

[14] የTackling the Frequent Forest Fire incidence in Ethiopia Forum for Environment Occasional ሪፖርት ቁጥር 2/2009

[15] በEthiopian Environment Review, FORUM FOR ENVIRONMENT, No, 2010

[16] በአክርማ/በአካባቢ እና ልማት ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር መጽሔት ቁጥር 28 2003 ዓ/ም

ብለው የገቡ ኢንቨስተሮች ደን ቆርጠው ጣውላ ሲያጓጓዙ እንደሚታዩ፤ በተወሰኑ ቦታዎች /ከበበቃ ደን ተያይዞ የሚገኘው ብርሃን ደን/ የሚመለከተው የክልል አካል ሳያውቅ ለጎማ ዛፍ ልማት በመሰጠቱ የተፈጥሮ ደኑ እየተመናመነ እና እየጠፋ እንደሚገኝ እነዚሁ በተለያዩ አካላት የተዘጋጁ የጥናት ጽሁፎች ይገልፃሉ[17]፡፡

71.የልማት ተግባራት የሀገሪቱ የተፈጥሮ ደን ሀብት ላይ ተገቢ ያልሆነ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩ ለደን በተለይም ለተፈጥሮ ደን ልማት ተግባር የሚሆኑ ቦታዎች በቅድሚያ ተጠንተው እንዲለዩ ባለመደረጉ በልማት ስም በተፈጥሮ የደን ህብት ላይ ጥቅም እና ጉዳቱን ባላገናዘበ ሁኔታ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስ አድርጓል (አባሪ 5.1-5.3 እና 6.1-6.4)፡፡ ይህ ሁኔታ ትኩረት ተሰጥቶት የተፈጥሮ ደን ሀብቱ ያለው ጠቀሜታ እና በልማት የሚመጣው ጥቅም እየተገናዘበ ሚዛናዊ የሆነ አሠራር ሊፈጠር ካልቻለ ለወደፊቱም ከዚህ በከፋ መልኩ በተፈጥሮ የደን ሀብቱ ላይ ጉዳት ሊደርስ ይችላል፡፡

## ስለደን ሀብት ጠቀሜታ እና አጠባበቅ ግንዛቤ መስጠትን በተመለከተ፡፡

### *ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቱን በመጠበቁ ረገድ ቀጥተኛ ተሳትፎ ላላቸው ባለድርሻ አካላት*

***ሀ/ ስለደን ሀብት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ግንዛቤ መስጠትን በተመለከተ፤***

72.ለሚመለከታቸው ወሳኝ ባለድርሻ አካላት በተለይም በተፈጥሮ ደን ሀብቱ ዙሪያ እና ውስጥ ለሚገኘው ኅብረተሰብ እና መንግስታዊ ለሆኑ አካላት የጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ዘርፉ ብዙ ጠቀሜታን በተመለከተ ግንዛቤ እንዲፈጠር ሊደረግ ይገባል፡፡

73.ከደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ ባገኘነው መረጃ መሠረት በክልሉ በሚገኙ 10 ቅድሚያ ከተሰጣቸው የመንግስት ደኖች መካከል በቦንጋ እና በሸካ ደን አካባቢ ለሚኖር ኅብረተሰብ የተፈጥሮ ደን ሀብት ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታን በተመለከተ ግንዛቤ ቢሰጥም አሁንም ህብረተሰቡ ኑሮውን ለማሟላት የተፈጥሮ ደኑን ዘለቄታዊ አጠቃቀምን ባልተከተለ መልኩ በመጠቀም ጉዳት እያደረሰበት እንደሚገኝ፤ የመንገድ ስራ ተቋራጮች፣ቴሌ፣ መብራት ኃይል በደን ሀብቱ ዙርያ ከክልሉ ጋር ተቀናጅተው እየሠሩ እንዳልሆነ እና ለነዚህ ባለድርሻ

አካላት የተፈጥሮ ደን ሀብቶችን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታን በተመለከተ በበቂ ሁኔታ ግንዛቤ አለመሰጠቱን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

74. በሁለቱም ክልሎች /በጭላሎ ጋለማ እና በቦንጋ/ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን አካባቢዎች ከሰበሰብነው መረጃ በአብዛኛው ትኩረት ተሰጥቶ ጥበቃ እና ክትትል የሚደረገው እንዲሁም ኅብረተሰቡ የመንግስት ጥብቅ ደን የሚለው በተከላ የለማውን ደን መሆኑን፤ በተፈጥሮ ደን ሀብቱ ዙሪያ ለሚገኝ ህብረተሰብ እና ባለ ደርሻ አካላት በዕቅድ ያልተያዙ አጋጣሚዎች በመጠቀም ግንዛቤ ለመስጠት ከመሞከር ውጪ ፕሮግራም እና ዕቅድ ተይዞለት ተከታታይነት ባለው መልኩ የተፈጥሮ ደንን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ በተመለከተ ግንዛቤ የማስጨበጫ ሥራ አለመሰራቱን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

75. በተለይ በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብት ይዞታዎች /በለጠጌራ፣አዳባ ዶዶላ/ ውስጥ እና አካባቢ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለያዩ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች (በJAICA, FARM-AFRICA) የተፈጥሮ ደን ሀብቱን ዘርፉ ብዙ ጠቀሜታን በተመለከተ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ የተሠራ እና ወደ 44 አሳታፊ የደን ጥበቃ ማኅበረሰቦችን በማደራጀት እና የተፈጥሮ ደን ይዞታውን በመጠን በመለየት እና በማከፋፈል የደኑን ብዝሀ ሕይወት እና ተፈጥሮአዊ ሁኔታ በማይጎዳ መልኩ ከደኑ የሚገኙ የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን የሚጠቀሙበት ሁኔታን ለማመቻቸት ጥረት የተደረገ ቢሆንም በአግባቡ ለመተግበሩ ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር ባለመደረጉ በአከባቢው የቡና ችግኝ ብቻ እየተፈላ ጥላ ዛፎችን ብቻ በመተው የተፈጠሮ ደኑ እየተመነጠረ ውስጡ እንዲተከል እየተደረገ መሆኑን፤ በዚህ ምክንት የተፈጥሮ ደኑ ብዝሀ ህይወት ጉዳት እያደረሰበተ እንደሚገኝ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል በጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱትን ለመከላከል ጥረት ሲደረግ እስከ ሞት ድረስ አደጋ እየደረሰ እንደሚገኝ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

76. የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ጉዳዩን አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ በየዓመቱ ከፌዴራል እስከ ክልል የአቅም ማጎልበቻ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ የአሰልጣኞች ስልጠና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ባለሙያዎች እንደሚሰጥ፤ በተመሣሣይ የክልል ባለሙያዎች ለወረዳ፣ የወረዳ ባለሙያዎች ደግሞ ለቀበሌና ለኅብረተሰቡ የአቅም ማጎልበቻና ግንዛቤ ማስጨበጫ

ስልጠና መስጠት እንዳለባቸው እንደአሠራር የተያዘ ጉዳይ እንደሆነ፤ ስልጠናው እስከ ሕብረተሰቡ ድረስ የሚደርስበት አጋጣሚ ግን አነስተኛ በመሆኑ ለወደፊቱ ትኩረት ሰጥተው ሊሠሩበት የሚገባ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

77. ከሰበሰብናቸው መረጃዎች ለመገንዘብ የተቻለው በዕቅድና ተከታታይነት ባለው መልኩ ድጋፍ፣ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ በፌደራልም ሆነ በክልሎች ደረጃ ቅድሚያ በተሰጣቸው የመንግስት ደኖች ዙርያ ለሚኖረው ህብረተሰብ እና ለሚመለከታቸው ባለደርሻ አካላት ስለ ተፈጥሮ ደን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ የግንዛቤ ማስጨበጫ እንዳልተሰጠ ነው፡፡ ይህ ተግባር በአግባቡ ቢከናወን በህገ ወጥ ሰፈራ እና በማገዶ ምክንያት የሚጨፈጨፈው ደን፣ በመንገድ ስራ፣ በኤለክትሪክ ዝርጋታ በመሳሰሉ በደኖች ላይ እየደረሰ ያለውን አደጋ መጠን ይቀንሰው ነበር፡፡ በተጨማሪም በደን ላይ አደጋ በሚያደርሱ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ላይ በወቅቱ ተመጣጣኝ የሆነ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ ይረዳ ነበር፡፡

### *ለ/ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ቀጣይነትን በተከተለ ሁኔታ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማግኘት ላይ ግንዛቤ መስጠትን በተመለከተ*

78. በተፈጥሮ ደን ሀብቱ ዙሪያ የሚገኘው ኅብረተሰብ የደን ሀብቱን ይዘት በማይጎዳ መልኩ ቀጣይነት ባለው መልኩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታ ላይ ግንዛቤ ሊያገኝ እና ተጠቃሚም ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡

79. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ እና በጉራጌ ዞን ግብርና መምሪያ በተፈጥሮ ደን ሀብቱ ዙሪያ የሚገኘው ኅብረተሰብ የደን ሀብቱን ይዘት በማይጎዳ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታ ላይ ግንዛቤ በተወሰኑ ቦታዎች ሀገር በቀል ባልሆኑ አካላት እንደሚሰጥ፤ ነገር ግን በመንግስት ደረጃ ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ ገበያ በማመቻቸት የአካባቢው ኅብረተሰብ ደኑን በማይጎዳ መልኩ ተጠቃሚ የሚሆንበት ስራ አለመሰራቱን ገልፀዋል፡፡ በዚሁ ክልል በከፋ ዞን ግብርና መምሪያ ካገኘነው መረጃ በባህላዊ ዘዴ ህብረተሰቡ በተወሰነ መልኩ እንደ የጫካ ቡና፣ ቅመማ ቅመም እና በደኑ ዛፍ ላይ የንብ ቀፎ በመስቀል ደኑን በማይጎዳ መልኩ ቀጣይነት በተከተለ መንገድ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ ለመፍጠር ሙከራ መደረጉን ነገር ግን በጥናት በተደገፈ ሁኔታ ለህብረተሰቡ እና ለአገሪቱ ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉ የደን ዝርያዎች ተጠንተው ባለመለየታቸው በዘመናዊ መልኩ የተሻለ ተጠቃሚ ሊሆን

የሚችልበት ሁኔታን ለመፍጠር በተጠናከረ መልኩ ግንዛቤ አለመስጠቱን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡



ፎቶ 7፤ ሀገር በቀል ዘፎች ባኅላዊ የንብ ቀፎዎች መስቀያ ሆነው ያገለግላሉ

80. በኦሮሚያ ክልል በናሙና መርጠን ባየናቸው አካባቢዎች በመናገሻ ሱባ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን አካባቢ በቂ ባይሆንም በፈረንሳይ መንግስት በተገኘ እርዳታ ወጨጫ፣ አጎዶ ሮጌ ለሚገኝ ኅብረተሰብ የንብ ቀፎ በማከፋፈል የተፈጥሮ ደኑን ሳይጎዳ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ጥረት የተደረገ ቢሆንም ቀጣይነት ባለው እና ሰፋ ባለ ሁኔታ አለመከናወኑን በደኑ ውስጥ የሚኖሩ ማኅበረሰቦች ደኑን እየመነጠሩ ወደ ሌሎቸ የመሬት አጠቃቀም እየቀየሩ መሆኑ (ፎቶ 8)፤ በለጠ ጌራ እና በአዳባ ዶዶላ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎች ውስጥ እና አካባቢ ለሚኖረው ኅብረተሰብ የደን ሀብቱን ይዘት በማይጎዳ መልኩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊያገኝ የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር የተለያዩ አጋጣሚዎችን በመጠቀም ካልሆነ በስተቀር ዕቅድ ተይዞለት ተከታታይ በሆነ መልኩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በመንግስት አካላት አለመሰራቱ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡



ፎቶ 6፤ በሱባ ቅድሚያ የተሰጠው ጥብቅ የመንግስት በደን ውስጥ በህገወጥ መልኩ የሰፈሩ ሰፋሪዎች የደን ሀብቱን መንጥረው ጫት ማልማታቸውን የሚያሳይ ፎቶግራፍ፡፡ /የካቲት 2004 ዓ/ም/

81.የሚመለከታቸው የግብርና ሚ/ር የሥራ ኃላፊዎች ሁኔታውን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ የፌዴራል ባለሙያዎች በየዓመቱ ከፌዴራል እስከ ክልል የአቅምና የግንዛቤ ማስጨበጫ የአሰልጣኝ ስልጠናዎች ለክልል ባለሙያዎች እንደሚሰጡ፤ በተመሣሣይ የክልል ባለሙያዎች ለወረዳ፣ የወረዳ ባለሙያዎች ደግሞ ለቀበሌና ለኀብረተሰቡ የአቅምና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና መስጠት እንዳለባቸው እንደ አሠራር የተያዘ ጉዳይ እንደሆነ ሆኖም ስልጠናው እስከ ሕብረተሰቡ ድረስ የሚደርስበት አጋጣሚ ግን አነስተኛ በመሆኑ ለወደፊቱ ሊሠሩበት የሚገባ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

82.በተቀናጀ፣ ቀጣይነት ባለው እና በታቀደ መልኩ ለሚመለከታቸው ወሳኝ ባለድርሻ አካላት በተለይም በተፈጥሮ ደን ሀብቱ ዙሪያ ለሚገኘው ኅብረተሰብ እና መንግስታዊ ለሆኑ አካላት የጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ዘርፉ ብዙ ጠቀሜታን መሠረት በማድረግ የደን ሀብቱን ይዘት በማይጎዳ መልኩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊያገኝ የሚችልበት ስልት ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ አለመሰራቱ ሀገሪቱ ከደን ሀብቷ ልታገኝ የምትችለውን ጠቀሜታ በሚጠበቀው መልኩ እንዳታገኝ ያደርጋል፡፡

### *ሐ/ የደን እሳት መከላከልን በተመለከተ ተግባራዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ የተሰጠ መሆኑን በተመለከተ፤*

83.በጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ዙሪያ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የደን እሳት መከላከልን በተመለከተ ተግባራዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሊሠጥ ይገባል፡፡

84. የደን እሳት ክስተት አደጋ ክትትል እና መከላከል ላይ የሕብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዳ ብሮሽርና /brochure/ ፖስተር ተዘጋጅቶ ለ9 ክልልሎችና አንድ መስተዳድር እንዲዳረስ እንደሚደረግ በአደጋ መከላከል እና ዝግጁነት በግብ ደረጃ ቢቀመጥም ተግባራዊ አልተደረገም። እንዲሁም በ2002 እና በ2003 ዓ/ም ለ200 የልማት ጣቢያ ሠራተኞችና 580 አርሶ አደሮች /አርብቶ አደሮች/ በደን እሳት መከላከል እና ቁጥጥር ግንዛቤ የማሳደግ በአደጋ መከላከል እና ዝግጁነት ዳይሬክቶሬት በኩል እንደሚከናወን እንደግብ ቢቀመጥም ተግባራዊ ስለመደረጉ በዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርቱ አልተገለጸም።

85. በቡታጅራ ቅድሚያ በተሰጠው የመንግስት ጥብቅ ደኖን ዙርያ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የደን እሳት መከላከልን በተመለከተ ተግባራዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ እንዳልተሰራ፤ በተወሰኑት ማለትም በቦንጋ እና በጭላሎ ጋለማ ደግሞ የደን እሳት መከላከልን በተመለከተ ተግባራዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ በተገኘው አጋጣሚ እና ተከታታይነት እና ቀጥይነት በሌለው መልኩ እንደሚሰጥ፤ በለጠ ጌራ፣ ባቢያ ፎላ፣ ሲግሞ፣ሰጠማ እና ጢሮ ቦተር የተባሉ ጥብቅ የተፈጥሮ ደኖች ዙርያ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የደን እሳት መከላከልን በተመለከተ ተግባራዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ስለመሰራቱ ከድስትሪክቶች ሪፖርት እንደቀረበላቸው፤ ሆኖም በለጠ ጌራ ደን ጽ/ቤት /ሸቤሳይት/ ያገኘነው መረጃ በስሩ ለሚያስተዳድረው ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ዙርያ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የደን እሳት መከላከልን በተመለከተ ተግባራዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ የተሠራ ቢሆንም ኀብረተሰቡ ከቃጠሎ ተጠቃሚ የሆነ ስለሚመስለው የደን ቃጠሎን በማጥፋት ከመተባበር ይልቅ ሆን ብሎ ወደ ደኑ እሳት የሚለቅና እንዲባባስ የሚያደርግ መሆኑን ከጽ/ቤቱ የደን ባለሙያ መግለጫ ለመገንዘብ ተችሏል።

86. የደን እሳት መከላከል የሚቻልበትን ዘዴ፤ በተለያዩ አማራጮች እና የተለያዩ መገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም ሕብረተሰቡን የማስተማር ሥራ ባለመሠራቱ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ማሳ በሚነሳና በግድ የለሽነት እና ሆን ተብሎ በደን ላይ በሚለኮስ እሳት ደኑ ሲቃጠል እሳቱን በአጭር ጊዜ በቁጥጥር ስር ለማድረግ በሚደረገው ጥረት በዙሪያው የሚኖሩ ማኅበረሰብም ሆነ የሌሎቸ ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በጣም ዝቅትኛ እንዲሆን በማድረግ የተፈጥሮ ደን ሀብቱ ለብዙ ቀናቶች እንዲቃጠል እና ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስበት እያደረገው ይገኛል።

***በአጠቃላይ ለሀገሪቱ ኅብረተሰብ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ጠቀሜታን በተመለከተ በተለያዩ የመገናኛ ብዙሃን የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠትን በተመለከተ***

87. በተለያዩ የሀገሪቱ ሥነ ምህዳሮች የሚገኙ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ጠቀሜታን በተመለከተ ህብረተሰቡ እነዚህን ውድ የሀገር ሀብቶች ቀጣይነትን በተከተለ ሁኔታ እንዴት ሊጠቀም እንደሚገባ የተለያዩ የመገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም ተከታታይነትና ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሊከናወን ይገባል፡፡

88. በደበብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ ይህን ተግባር በተመለከተ የመገናኛ ብዙሀን አልፎ አልፎ ሲመጡ መረጃ ከመስጠት ውጪ በዕቅድና ቀጣይነት ባለው መልኩ የተለያዩ የመገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም ሕብረተሰቡን የማስተማር ስራ እንዳልተሰራ ገልፀዋል፡፡

89. የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ ከኢትዮጵያ ሬድዮ ድርጅት ጋር በመተባበር ለብቻው ሳይሆን ከተፈጥሮ ሀብት ልማት ሥራዎች ጋር በማቀናጀት በተለያዩ የሀገሪቱ ሥነምህዳሮች የሚገኙ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ጠቀሜታ፣ እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ህብረተሰቡ እነዚህን ውድ የሀገር ሀብቶች ቀጣይነትን በተከተለ ሁኔታ እንዴት ሊጠቀም እንደሚገባ ግንዛቤ ለመስጠት በሣምንት አንድ ጊዜ መርሐ ግብር ተይዞ በተከታታይ የሚተላለፍ መልእክት እንዳለ፣ ወቅታዊ የደን ሁኔታዎች ሲገኙም ለምሣሌ የችግኝ ተከላ ጊዜ ሚዲያዎች በመጠቀም ሰፊ መልእክት እንደሚተላለፍ፣ ሆኖም በዚህ ረገድ በቂ ሥራ ተሠርቷል ማለት እንደማይቻል፣ ከፌዴራል እስከ ክልል ብሎም እስከ ሕብረተሰቡ ድረስ የሚዲያ ስርጭት ለማዳረስ የሚጠይቀው ወጪ ቀላል አለመሆኑ ችግር ተደርጎ እንደሚታይ ገልፀዋል፡፡

90. ኅብረተሰቡ ስለተፈጥሮ ደን ሀብት መተኪያ የሌለው ጠቀሜታ ግንዛቤው እንዲዳብር የሚደረገው ጥረት ውስን መሆን ይህን ውድ የሀገር ሀብት ለመጠበቅ በግሉም ሆነ በጋራ ሊያበረክታቸው የሚገቡ ተግባራትን በመለየት አስተዋጽኦ እንዳያደርግ፣ በፍትህና በውሳኔ ሰጪ አካላት በኩልም ተገቢ ሚዛናዊ ፍርድ እንዳይሰጥ እና የዚህን ውድ ሀብት ልዩ ጠቀሜታ ያገናዘበ ውሳኔ እንዳይወሰን በማድረግ በተፈጥሮ ደን ሀብቱ ላይ እየደረሰ ያለውን ውድመት ለመቀነስ እና ብሎም ለማግታት የሚደረገው ጥረት ውጤታማነት ላይ የጎላ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

## የደን ሀብትን የሚመለከቱ መረጃዎች አደረጃጀት እና ልውውጥን በተመለከተ

### የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚያስችል ሥርዓትን በተመለከተ፤

91.የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን የሚመለከቱ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው የፌደራል፣ የክልል እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በተፈለገው አይነት፣ መጠን እና ወቅት ለመለዋወጥ የሚያስችል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ሊኖር እና መደበኛና ቀጣይነት ባለው መልኩ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

92.በደን ዙሪያ በተለያዩ አካላት የተጠኑ ጥናቶች የሀገሪቱን የደን ሀብት ሁኔታ የሚያሳዩ ወቅታዊ መረጃዎች በየጊዜው እየተጠናቀሩ እንደማይያዙ፤ ያሉት መረጃዎችም ከ20 ዓመታት በላይ የቆዩ እና እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ መሆናቸውን እንዲሁም የደን ቀጥተኛ እና ተዘዋዋሪ ጥቅሞችን በግልጽ የሚያሳይ የመረጃ ቋት አለመኖሩን ይገልፃሉ[18]፡

93.በደበብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ በፌደራል ደረጃም ሆነ በክልል ከሚገኙ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን በተመለከተ የማያቋርጥና መደበኛ የሆነ የመረጃ ልውውጥ እንደማይደረግ፤ ለመረጃ ልውውጡ የሚያገለግሉ የመረጃ መለዋወጫ ቅጾች በጥናት አለመዘጋጀታቸውን ተገንዝበናል፡፡ በዚሁ ክልል በከፋ ዞን ግብርና መምሪያ ራሳቸው ያዘጋጁት የመረጃ መለዋወጫ ፎርም ቢኖራቸውም ፎርሙ ደረጃውን የጠበቀ፣ በጥናት የተደገፈና በማዕከል የተዘጋጀ አለመሆኑን ተረድተናል፡፡ በጉራጌ ዞን ግብርና መምሪያ የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን በተመለከተ የመረጃ ልውውጥና ቅብብሎሽ ከሚመለከታቸው የክልል አካላት ጋር እንደሚደረግ ሆኖም ይህ መረጃ ለደን ለብቻው ሳይሆን በተፈጥሮ ሀብት ጥበቃና ልማት ውስጥ ተካቶ እንደሚተላለፍ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

94.በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በአርሲ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት ቅርንጫፍ ጽ/ቤት፣ አዳባ ዶዶላ እና በጭላሎ ጋልማ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሁኔታን

---

[18] CHANGE DETECTION OF NATURAL HIGH FORESTS IN ETHIOPIA USING REMOTE SENSING AND GIS TECHNIQUES Source: Matthias REUSING - Land Use Planner German Technical Cooperation (GTZ), Ethiopia German Development Service (DED), Ethiopia Land Use Planning and Resource Management Project in Oromia Region (LUPO) atomatthias@hotmail.com

በተመለከተ በየወሩ ለአርሲ ነገሌ ደንና ዱር እንስሳት ጽ/ቤት ሪፖርር እንደሚያቀርብ እና ከሚመለከታቸው የክልልና የዞን አካላት ጋር የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን የሚመለከቱ መረጃዎች በማያቋርጥና መደበኛ በሆነ መልኩ እንደሚለዋወጡ ገልፀዋል፡፡ በዚሁ ክልል በጅማ ዞን ደንና ዱር እንስሳት ጥበቃ ጽ/ቤት የደን ሀብት ልማትን በተመለከተ ከሚመለከታቸው የፌደራልና የክልል አካላት ጋር የማያቋርጥና መደበኛ የሆነ የመረጃ ልውውጥ እንደማይደረግ በተጨማሪም ቅጾች ወይም ፎርማቶች  በማዘጋጀት ጥቅም ላይ እንዲውሉ አለመደረጉን ተረድተናል፡፡ በለጠ ጌራ ደን ጽ/ቤት ሽቤሳይት በፌደራልና በክልሎች የደን ሁኔታን በተመለከተ ለመረጃ መለዋወጫ የሚያገለግሉ ቅጾች ያሉ መሆኑን ከሚመለከታቸው  የክልልና የዞን አካላት ጋር በተለያዩ አጋጣሚዎች በደን ዙርያ ውይይት የሚያደርጉ ቢሆንም የደን ሀብት ልማትን በተመለከተ መደበኛ በሆነና በማያቋርጥ ሁኔታ የመረጃ ልውውጥ እንደማይደረግ ገልፀዋል፡፡

## ለደን ልማት ተግባር በተከለሉ አካባቢዎች ላይ የተተከሉ ችግኞችን የሚመለከቱ መረጃዎችን በተመለከተ

95.በመንግስት ለደን ልማት ተግባር በተከለሉ አካባቢዎች ላይ የተተከሉ ችግኞችን አይነት እና መጠን፣ ከተከላ ጊዜአቸው ጀምሮ በየደረጃው የተደረገላቸውን እንክብካቤ እና ጥበቃ፣ ለተተከሉበት ዓላማ ለመዋላቸው ተከታታይነት ያለው ተግባር ለማከናወን የሚያግዝ ጥናት መደረጉን፣ በጥናቱ መሠረት የማስፈጸሚያ ዕቅድ መዘጋጀቱን፤ በአጠቃላይ ክትትል በማድረግ ከተተከሉ ችግኞች፣ የጸደቀውን መጠን፣ እያስገኙ ያለውን ጠቀሜታ የሚገልጽ መረጃ በአግባቡ በመያዝ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡

96.በተፈጥሮ ደን ሀብት ዙሪያ በተለያዩ ባለድርሻ አካላት የተዘጋጁ ጥናታዊ ጽሁፎች የሀገሪቱን የደን ሀብት የሚመለከቱ መረጃዎችን በተመለከተ ዋናው ችግር ግልፅና ታማኝ የመረጃ ምንጭ አለመኖሩ እንደሆነ ይገልጻሉ[19]፡፡ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ ችግኞች በየግዜው እንደሚተከሉ ነገር ግን  ምን ያህል እንደፀደቁ እና እንዳልፀደቁ ያለው ውጤት ተለይቶና ተጨምቆ በዶክመንት መልክ የማስቀመጥ ትልቅ ድክመት መኖሩን፤ በደን

---

19 በEthiopian Environment Review, FORUM FOR ENVIRONMENT, No, 2010

ዙሪያ የተሰሩ ሥራዎች መረጃዎች ተጠናቅረው የማይቀመጡ መሆኑን፣ በሄክተር የተተከለ የደን ሽፋን ለግብርና ሚ/ር በተፋሰስ ዙሪያ ከተሠሩ ሥራዎች ጋር በማጠቃለል ሪፖርት ከማድረግ ውጪ ክትትል በማድረግ ከተተከሉ ችግኞች ምን ያህሉ እንደፀደቁ በሪፖርቱ የማይካተቱ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ በዚሁ ክልል በከፋ ዞን ግብርና መምሪያ ችግኞች ከተተከሉ በኋላ ምን ያህሉ እንደፀደቁ እና በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ክትትል የማይደረግ መሆኑን፣ በተጨማሪም የሚተከሉት ችግኞች ለአካባቢ ጥበቃና ለፍጆታ ቢሆንም ለተተከሉበት ዓላማ ስለመዋላቸው ጥናት አለመደረጉን፤ ለዚህም ዋናው ምክንያት የአቅም ውሱንነት እንደሆነ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

97. በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን የደንና ዱር እንስሳት ጽ/ቤት የሥራ ኃላፊዎች እስካሁን በደኖች ላይ ጥናት ያልተደረገ መሆኑ ነገር ግን ጥናት ለማከናወን በሂደት ላይ መሆናቸውንና በዚህ መልክ ደኑ እያስገኘ ያለውን ጠቀሜታ በተመለከተ የተያዘ መረጃ አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡ የአርሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በጥብቅ የተፈጥሮ ደን ውስጥ የፈረንጅ ጽድ፣ ፓይነስ እና በመጠኑ ግራቪሊያ እና ባሕር ዛፍ ዝርያዎች የተተከሉ መሆኑን፣ በአነስተኛ መጠን አገር በቀል ዛፎች ማለትም እንደዋንዛ፣ ኮሶ እና የአበሻ ጥድ መተከላቸውን፣ ተገቢው እንክብካቤ የሚደረግላቸው መሆኑን እና ከ90 % በላይ እንደፀደቁ ለኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት በየወቅቱ ሪፖርት እንደሚደረግ ገልፀዋል፡፡

98. የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ይህን ጉዳይ በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ በዕቅድ የተመራ ቀጣይነት ያለው የመረጃ ልውውጥ አለ ለማለት እንደማይቻል ለዚህም ምክንያቱ ለዚህ ሥራ የሚሆን በጀትና አደረጃጀት ማለትም ራሱን የቻለ የደን ኢንቬንተሪ ቲም በፌዴራልም ሆነ በክልል አለመኖሩ እንደሆነ፤ ነገር ግን ከመ/ቤቱ ውጭ ሊያግዙ የሚችሉ የልማት አጋሮች በማፈላለግ ስራው ሊሰራ እንደሚችል እምነት ስላላቸው ከዓለም የምግብ ድርጅት ጋር በመተባበር ሥራውን መሥራት የሚቻልበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ጥረት እየተደረገ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

99. በሀገር አቀፍ ደረጃ የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመለዋወጥ የሚያስችል ሥርዓት አለመዘርጋቱ በልማት የሚተከሉ ችግኞች የተተከሉበትን ቦታ፣ አይነት እና መጠን፣ ከተከላ ጊዜአቸው ጀምሮ በየደረጃው

ሊደረግላቸው የሚገባ እንክብካቤ የተደረገላቸው መሆኑን ለመከታተል፤ ከተተከሉ ችግኞች የጸደቀው መጠን ምን ያህል እንደሆነ፣ ለተተከሉበት ዓላማ መዋላቸውን እና እያስገኙ ያለውን ጠቀሜታ ለማወቅ አያስችልም፡፡ በይበልጥም በሀገሪቱ የተፈጥሮ ደን ሀብት ላይ እየደረሰ ያለው ጉዳት በወቅቱ እንዳይታወቅ እና የሚመለከታቸው አካላት ሁኔታውን ተገንዝበው ተገቢውን እርምጃ እንዳይወስዱ የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ የአገሪቷ የደን ሽፋን በየዓመቱ ምን ያህል እንደጨመረና እንደቀነሰ በትክክል ለማወቅ አያስችልም፡፡

## የደን እሳት አደጋ ክስተትና መከላከል መረጃ ልውውጥን በተመለከተ

100. የደን እሳት አደጋ ክስተትና መከላከልን በሚመለከት ከሀገራዊ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የስራ ሂደት ጋር የመረጃ ልውውጥ ማድረግ ይገባል፡፡

101. በናሙና በመለየት ባየናቸው በደበብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እና በኦሮሚያ በሔራዊ ክልላዊ መንግስታት የደን እሳት አደጋ ክስተትና መከላከልን በተመለከተ ተከታታይነትና ቀጣይነት ባለው መልኩ ከሀገራዊ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የሥራ ሂደት ጋር የመረጃ ልውውጥ እንደማይደረግ ከሰበሰብናቸው መረጃዎች ለመገንዘብ ችለናል፡፡

102. የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ይህን ጉዳይ በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የደን እሳት አደጋን በተመለከተ ወቅታዊ እና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ ከሀገራዊ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የስራ ሂደት ጋር መኖሩ እነዚህ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎችን ለመድረስ ካለው ርቀት እና አስቸጋሪነት አንፃር ጉዳቱን በተሻለ ብቃት ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ያለው አቅም የተሻለ እንዲሆን የጎላ አስተዋጽኦ እንዳለው እና ለወደፊት ትኩረት እንደሚሰጠው ገልጸዋል፡

## በደን ሀብት ዙሪያ ሊከናወኑ የሚገቡ ተግባራትን ለማከናወን ያለውን አደረጃጀትና የሰው ኃይልን በተመለከተ

## አጠቃላይ አደረጃጀት እና የሰው ኃይልን በተመለከተ፤

103. በሚኒስቴር መ/ቤቱም ሆነ በየደረጃው በተዋረድ በሚገኙ አስፈጻሚ አካላት የደን ልማትና ጥበቃን በተመለከተ በአዋጅ የተጣለበትን ኃላፊነት የሚያከናውን አካል ሊዋቀር እና በተገቢው የሰው ኃይልና ቁሳቁስ ተደራጅቶ ፖሊሲውን የማስፈጸም ተግባር ሊያከናውን ይገባል፡፡

104. የደን መዋቅር ለረጅም ዘመናት በፍጥነት የሚቀያየር እና ያልተረጋጋ እንደነበር በአሁኑ ወቅት ደግሞ በፌደራል ደረጃ ይህንንም ተግባር ለማከናወን በ5 ባለሙያዎች ብቻ የተደራጀ መሆኑ፤ በክልሎችም የደን ልማት እና ጥበቃን የሚያከናውን አካል በበቂ አደረጃጀት እና ባለሙያ ያልተጠናከረ መሆኑ በደን ዙሪያ በተከናወኑ የተለያዩ ጥናቶች ተገልጿል[20]፡፡

105. በደበብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች በምግብ እህል እራስን ለመቻል የሚደረገው ጥረት እና የደን ሀብትን ለማልማት እና ለመጠበቅ የሚደረገው ጥረት ሲነፃፀር በየጊዜው እየጨመረ ያለውን የህዝብ ቁጥር ለመመገብ የሚፈለገውን ያህል የምግብ እህል ለማምረት የደን ይዞታዎች ወደ እህል እርሻ ቦታነት የሚቀየርበት ሁኔታ መኖሩን፣ ሁለቱ ተቃራኒ ተግባራት በአንድ አስፈጻሚ አካል እየተከናወኑ እንደሆነ፤ ይህንን ለመቋቋምና በደን ላይ የሚደርሰውን አደጋ ለመከላከል ጠንካራ የደን መዋቅር አለመኖሩን፤ በተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃ የሥራ ሂደት ውስጥ የደን ጉዳይን የሚከታተል አካል በኬዝ ቲም ደረጃ እንኳ አለመቋቋሙንና በአራት ባለሙያ ብቻ እየተሰራ ያለ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

106. በዚሁ ክልል በከፋ ዞን ግብርና መምሪያ መዋቅሩ ያለ ቢሆንም በቂ አለመሆኑን፤ በዞኑ የሚገኘውን የቦንጋ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ለመጠበቅም ሆነ ለማስተዳደር ለብቻው የተለየ የሰው ኃይልም ሆነ አደረጃጀት ባለመኖሩ በባለቤትነት

---

[20] በNatural resource management and environmental protection : (የኢትዮጵያ የሠላም፣ የልማትና የዲሞክራሲ ሕዝባዊየምክክር መድረክ- በአቶ ደምሰው በቀለበው ፅሁፍ እና በEthiopian Environment Review, FORUM FOR ENVIRONMEN በቀረበው ፅሁፍ

የሚያስተዳድረው አካል የሌለ በመሆኑ ጉዳት እየደረሰበት እንደሆነ፤ በጉራጌ ዞን ግብርና መምሪያ በዞን ደረጃ እና በ13ቱ ወረዳዎች የደን ተግባር የሚያከናውኑ አንድ አንድ ባለሙያ የተመደቡ ቢሆንም እንዲሠራ ከሚጠበቀው ተግባር አንጻር በቂ እንዳልሆነ እና የደን ጥበቃና ልማትን ለማከናወን በቂ የሆነ የሎጂስቲክ አቅርቦት አለመኖሩን የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

107. በኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ኢንተርፕራዝ ስር ያሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሁኔታ ሲታይ በዞን ደረጃ በቂ መዋቅር ቢኖርም ወደታች የተፈጥሮ ደን ሀብቱ ባለበት ቦታ ላይ የተሟላ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል አለመኖሩን፣ በተለይ በወረዳ ደረጃ አንድ ሰው ብቻ ደን ነክ የሆኑ ጉዳዮችን በተመለከተ መመደቡን፤ የአርሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በቂ የደን ባለሙያዎች እንዳሏቸው የገለጹ ቢሆንም በሌሎቹ አካባቢዎች የሰው ኃይል እጥረት እንዳለና ለማሟላት ጥረት ቢደረግም ሠራተኞች በተደጋጋሚ የሚለቁበት ሁኔታ እንደሚታይ እና በደን ሀብቱ ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን ለመከላከል የተሟላ ቁሳቁስ እጥረት መኖሩን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

108. ይህን ሁኔታ በተመለከተ የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የሥራ ኃላፊዎች ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ በፌደራልም ሆነ በክልሎች ደረጃ ያሉትን የስራ መደቦች በባለሞያ ማሟላት ከተቻለ ያለው የደን መዋቅር የሀገሪቱን የደን ሀብት ለማልማት፣ ለመጠበቅ እና ዘላቂነትን የተከተለ አጠቃቀም እንዲኖር ለማድረግ ሊከናወኑ የሚገቡ ተግባራትን ለማከናወን በቂ ነው ብለው እንደሚያምኑ ገልፀዋል፡፡

109. ሆኖም በደንን መውደም እና መመናመን ምክንያት የሚወጣውን በካይ ጋዝ (GHG) ለመቀነስ መፍትሄ ያመጣል ተብሎ ሚኒስቴር መ/ቤቱን በማሳተፍ በተደረገ ጥናት[21] ላይ በኢትጵያ ጠንካራ የሆነ የደን ተቋም እንደሌለና ተቋሙ መጠናከር እንዳለበት ተቀምጧል፡፡ በመሆኑም በሀገሪቱ የደን ሀብት ዙሪያ ሊከናወኑ ከሚገባቸው ተግባራት አሁን ያለው አደረጃጀት እንደገና ቢታይ በተፈጥሮ ደን ሀብቱ ላይ በስፋት እየደረሰ ያለውን ጉዳት ለመቀነስ አስተዋጽኦ ይኖረዋል የሚል እምነት አለን፡፡

[21] READINESS PREPARATION PROPOSAL ASSESSMENT NOTE

## የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መረጃ የሚያቀነባብሩና የሚያሰራጩ አካላት በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መሣሪያዎች መጠናከራቸውን በተመለከተ

110. በፌደራልና በክልሎች በየደረጃው የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መረጃ የሚያቀነባብሩና የሚያሰራጩ አካላት በሰው ኃይልና በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና መሣሪያዎች እንዲጠናከሩ ሊደረግ ይገባል፡፡

111. በደበብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ፣ በጉራጌ ዞን ግብርና መምሪያ፣ በከፋ ዞን ግብርና መምሪያ፣ እንዲሁም በኦሮሚያ ደንና ዱር እንስሳት ኢንተርፕራይዝ፤ በጅማ ዞን ደንና ዱር እንስሳት ጥበቃ ጽ/ቤት፣ በመናገሻ ሱባ ዲስትሪክት ጽ/ቤት፣ በለጠ ጌራ ደን ጽ/ቤት /ሸቤሳይት/፣ በአርሲ ደንና ዱር እንስሳት ድርጅት ቅርንጫፍ አዳባ ዶዶላ ዲስትሪክት እና በጭላሎ ጋለማ የደንና ዱር እንስሳት ጥበቃና ልማት ዲስትሪክት ጽ/ቤት የመንግስት ደኖች በተመለከተ በየደረጃው የደን ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም መረጃ የሚያቀነባብሩና የሚያሰራጩ አካላት በሰው ኃይልና በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና መሣሪያ እንዲጠናከሩ አለመደረጉን፤ ሆኖም የአርሲ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በሰው ኃይል ለማጠናከር ጥረት በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡ ተፈጥሮ ሀብቱ ለሀገሪቱ የተፈጥሮ ሚዛን መጠበቅ፣ ለኢኮኖሚያዊና ማኀበረሰብአዊ አገልግሎት ካለው መሠረታዊ አስተዋጽኦ አንፃር ይህን ሥራ የሚሠሩ አካላት ተገቢው አደረጃጀት እንዲኖራቸው እና በተገቢው የሰው ኃይልና ቁሳቁስ እንዲደራጁ ካልተደረገ የደን ፖሊሲውን የማስፈጸም አቅም አይኖራቸውም፡፡

112. ይህንንም በተመለከተ ለፌደራል ግብርና ሚ/ር ለቀረበው ቃለ መጠየቅ በተሰጠው መልስ የደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም መረጃ የማያቀነባብሩ እና የሚያሰራጩ አካላት በሰው ኃይልና በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና መሣሪያ እንዲጠናከሩ ለማድረግ እና ይህንን ሥራ በዕቅድ ውስጥ አካቶ ለመሥራት በቂ የሰው ኃይልና አደረጃጀት የሌላቸው በመሆኑ በራሳቸው አቅም መፍጠር እንደነበረባቸው ገልፀዋል፡፡

113. በመሆኑም በፌደራል ደረጃም ሆነ በክልሎች በደን አዋጅ እና ፖሊሲ ላይ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ እንዲሁም በየደረጃው በክልል እና በወረዳ ደረጃ ለሚገኙ አካላት የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር በብቃት እና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለማከናወን እና

የሀገሪቱን የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ እና ቀጣይነትን ያገናዘበ አጠቃቀም ልምድን ለማዳበር  የሚያችል አካል በበቂ አደረጃጀት እና ባለሙያ ተጠናክሮ ተደራጅቷል ለማለት አያስችልም፡፡

## በደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ላይ የግል ባለ ሀብቱን እና ሌሎች የህረተሰብ ክፍሎች ተሳትፎን በተመለከተ

114. በደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ላይ በግለሰብ፤ በማህበርና በባለሀብቶች ደረጃ የሚደረግ ተሳትፎ እንዲጠናከር ተገቢው ጥረት እና ድጋፍ ሊደረግ እንዲሁም በእነዚህ አካላት ስር የሚገኙ የደን ይዞታዎች መጠንና የአጠቃቀም ሁኔታን የሚያሰዩ መረጃዎችን በማሰባሰብ  በአግባቡ እንዲያዙ ሊደረግ ይገባል፡፡

115. በኦዲቱ ወቅት እንደተገነዘብነው በአጠቃላይ በደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ዙሪያ በግለሰብ፤ በማህበርና በባለሀብቶች ደረጃ  የሚደረግ ተሳትፎን የሚያመለክቱ መረጃዎች ለማግኘት አልተቻለም፡፡ ሲሆን፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት ግብርና  ቢሮ በግል፣ በማህበር እና በባለሀብቶች የተያዘ የደን መጠንና የአጠቃቀም መረጃ በተሟላ ሁኔታ እንዳልተያዘ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊ ገልፀዋል፡፡ ሚኒስቴር መ/ቤቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ በግል፤ በማህበርና በባለሀብቶች የተያዘ የደን የይዞታ መጠንና የአጠቃቀም ሁኔታን የሚመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብ  በአግባቡ ለማያዝ እና ክልሎች በዚህ መልኩ እንዲይዙ ክትትልና ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል የሰው ኃይልና አደረጃጀት እንደሌለው ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ የሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች ገልፀዋል፡፡

116. በመሆኑም የሀገሪቱን የደን ሀብት በማልማት፣ በመጠበቅ እና ዘላቂነትን በተከተለ ጥቅም ላይ የማዋል ልምድን ከማዳበር አኳያ የግል፤ የማህበር እና የባለሀብቶች ድርሻ ሰፊ ቢሆንም በእነዚህ አካላት የተያዘ የደን የይዞታ መጠንና የአጠቃቀም ሁኔታን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለማግኘት ባለመቻሉ ተሳትፎአቸው በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማወቅ አያስችልም፡፡

# ክፍል ሦስት

## መደምደሚያ

117. ሀገራች በአካባቢ ላይ የሚደርሰውን ተጽዕኖ በመቀነስ ላይ ያተኮረ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ለመገንባት ለያዘችው ወሳኝ ዓላማ የደን ሀብትን ማልማት፣ መጠበቅ እና ቀጣይነትን የተከተለ አጠቃቀም ልምድን የማጎልበት ተግባር ወሳኝ አስተዋጽኦ እንዳለው በማመን እንደዋነኛ መሠረታዊ ተግባር ተቀምጧል[22]፡፡

118. አረንጓዴ ኢኮኖሚ የመገንባት ዓላማን ለማሳካት የሚረዱ ከአካባቢ ጥበቃ ጋር የተያያዙ የተለያዩ አዋጆች እና ፖሊሲዎች በተለያዩ ጊዚያት የወጡ ቢሆንም ተግባራዊ በማድረጉ ረገድ ግን ድክመቶች ይታያሉ፡፡ በ1999 ዓ.ም የደን አዋጅ የወጣ እና ፖሊሲም የጸደቀ ቢሆንም[23] እነዚህን በፌዴራል ደረጃ የተዘጋጁ አዋጅ እና ፖሊሲ ለመተግበር የሚያስችሉ ደንብ እና መመሪያዎች አለመዘጋጀታቸው እና ጥብቅ የተፈጥሮ ደን አካባቢ ተብለው የተለዩት ቦታዎች የህጋዊ ሰውንት እንዲኖራቸው ተደርጎ ድንበራቸው እንዲከለል እና በተለይ ብዝሀ ሕይወትን ከመጠበቅ አንፃር ያላቸው የማይተካ ወሳኝ ሚና ልዩ ትኩረት እንዲሰጠው አለመደረጉ፤

- የደን ይዞታዎች ላይ በሚከናወኑ ጥቅም እና ጉዳታቸው በአግባቡ ያልታየ እና የአካባቢ ተጽዕኖን ያላገናዘቡ የልማት ተግባራት እንዲያከናውኑ፡፡
- ከሀገሪቱ ህዝብ ቁጥር መጨመር ጋር በተያያዘ እና በተለያዩ አስገዳጅ ሁኔታዎች በሚከሰት የህገወጥ ሠፈራ፣ ወዘተ በሚደረጉ መስፋፋቶች እና

በእሳት አደጋዎች በደን ሀብቱ በተለይም በጣም ውስን በሆኑ አካባቢዎች ብቻ በሚገኙ እና አሉ የተባሉትን የሀገሪቱን የብዝሀ ሕይወት ሀብቶች አከማችተው ይዘው በሚገኙ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ላይ የሚደርሱ ውድመቶችን በከፍተኛ ሀኔታ እንዲባባሱ፣ ዘላቂነት ባለው ሁኔታ ኢኮኖሚያዊም ሆነ ሌሎች ማኀበረሰባዊ አገልግሎቶችን ማግኘት እንዳይችሉ፤ በአጠቃላይ የሀገሪቱን የደን ሀብት የሚመለከቱ ተቀባይነት ያላቸው ወቅታዊ መረጃዎች ለመያዝ እንዳይቻል አድርጓል፡፡

---

[22] Ethiopia's Climate – Resilient Green Economy, November 2011

[23] የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምፖሊሲ፣ ስትራቴጂና አዋጅቁጥር 542/1999

119. በሀገር አቀፍ ደረጃ በየዓመቱ ችግኞች የሚተከሉ ቢሆንም የተተከሉበት አካባቢ፣ የቦታው ስፋት፣ ምን ያህልና አይነት እንደተተከለ፣ የፀደቀው መጠን፣ የታለመለትን አገልግሎት እስኪሰጥ ድረስ እየተደረገለት ያለው ክትትልን የሚያሳዩ መረጃዎች ተጠናቅረው የማይቀመጡ መሆኑን፣ የዘፍ ችግኞች ከተተከሉ በኋላ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ በቂ ክትትል የማይደረግ መሆኑን፣ በተጨማሪም የሚተከሉት ችግኞች ለተተከሉበት ዓላማ ስለመዋላቸው ጥናት አለመደረጉን፤ ለዚህም ዋናው ምክንያት የአቅም ውሱንነት እንደሆነ ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለመገንዘብ ተችሏል።

120. በተለይ የተፈጥሮ ደን ቦታዎች በአብዛኛውም ገና በመጠናት ላይ ያለውን የሀገሪቷን የብዝሃ ህይወት ሀብት ስብጥር በስፋት የያዙ ከመሆናቸው አንጻር ተገቢው ጥበቃ እና ልማት በፍጥነት ካልተደረገላቸው ለሀገሪቱ ዕድገት ከፍተኛ እና የማይተካ ጥቅም ሊሰጥ የሚችል የብዝሀ ሕይወት ሀብትን እንደያዙ በአግባቡ ሳይታወቁ እና ጥቅም ላይ ሳይውሉ በአጭር ጊዜ ከገጸ ምድር ሊጠፉ የሚችሉበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል። ለዚህም እንደ መሠረታዊ ችግር የሚታየው ለሀገሪቱ የደን ሀብት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በአግባቡ ለማልማት፣ ለመጠበቅ እና ቀጣይነት ያለው የአጠቃቀም ልምድ እንዲዳብር ለማድርግ የሚያስችል ተግባርን ማከናወን የሚያስችል አደረጃጀትና በቂ የሰው ኃይል አለመፈጠሩ እንደሆነ በደን ዙሪያ ከተዘጋጁ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎች[24]፣ የውይይት መድረኮች ቃለ ጉባኤዎች እንዲሁም ከሚኒስቴር መ/ቤቱ እና ከሌሎች ዋነኛ ባለድርሻ አካላት በተጨማሪም በመስክ ጉብኝት በክልል፣ በዞን እና የጥብቅ ደን ሀብቶቹ ባሉበት ቦታ ከሰበሰብናቸው መረጃዎች ለመገንዘብ ችለናል።

[24] Readiness Preparation Proposal Assessment Note

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳብ

121. የደን ሀብት ለአንድ ማኅበረሰብ ብሎም ለሀገር ህልውና የሚሰጠው ዘርፈ ብዙ (multi purpose) ጠቀሜታ ከፍተኛ እና በገንዘብ የማይለካ በመሆኑ በስፋት እየታየ ያለውን የደን ሀብት መኅሳቆል እና መውደም ለመቀነስ መንግስት ትኩረት በመስጠት በአግባቡ ለማልማት፣ ለመጠበቅ እና ዘላቂነትን የተከተለ አጠቀምን ለማጎልበት ያወጣቸውን አዋጅ እና ፖሊሲ ለማስፈጸም የሚረዱ አግባብነት ያላቸው ደንብና መመሪያዎች በፌዴራልም ሆነ በክልል ቅድሚያ ትኩረት ተሰጥቷቸው እንዲዘጋጁ እና ጸድቀው ተግባራዊ እንዲሆኑ በማድረግ ቀጣይነት ባለው መልኩ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርጉ ይገባል፡፡

122. የደን ሀብቱን በአግባቡ ለማልማት፣ ለመጠበቅ እና ቀጣይነትን መሠረት ያደረገ አጠቃቀም ልምድ እንዲጠናከር እና እንዲስፋፋ ለማድረግ እንዲቻል በደን አዋጅ እና ፖሊሲ ላይ የተቀመጡ ተግባራትን ለመተግበር ብቃት ያለው አደረጃጀትን በጥናት ማዋቀርን እና ከፍተኛ በጀት ይጠይቃል፡፡ ሆኖም የደን ሀብቱን በአግባቡ ማልማት ማስተዳደር ከተቻለ በካርበን ንግድ ከዓለም አቀፍ ኅብረተሰብ፣ የደን ሀብት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ ከሆኑ አካላት ማለትም ከመስኖ፣ ከኃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል፣ ወዘተ ቀረጥ ሊሰበሰብ የሚችልበትን ሁኔታ በማመቻቸት ከዓለም አቀፍም ሆነ ከሀገር ውስጥ ምንጭ በቂ የሆነ የገንዘብ ምንጭ በማስገኘት ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ ዕድገት የጎላ አስተዋጽኦ ለማበርከት የሚያስችል አቅም ለመፍጠር ይቻላል፡፡ በመሆኑም እነዚህን እና ጉዳት እየደረሰበት ያለውን የአገራችን የደን ሀብት ከተጋረጠበት መጠነ ሰፊ ጥፋት ለማዳን የደን አዋጅ እና ፖሊሲ ላይ የተቀመጡ ተግባራት እና ኃላፊነቶች የፌዴራል አወቃቀሩን ተከትለው በሁሉም ባለድርሻ አካላት በስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ ዕቅዳቸው ውስጥ በማካተት ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡

123. በተፈጥሮ ደን ሀብቱ ላይ እየደረሰ ያለውን መጠነ ሰፊ ጉዳት ለመቀነስ እና የሀገሪቱን የብዝሀ ህይወት ሀብት የያዙ ቅድሚያ የተሰጣቸው የተፈጥሮ ደን ቦታዎችን ለመጠበቅ በተለየ ሁኔታ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በየደረጃው የሚገኙ

የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ የመሬት አስተዳደር አዋጅን መሠረት በማድረግ

- ❖ በተለይ ጥበቃ እንዲደረግላቸው የተለዩት ጥብቅ የተፈጥሮ ደን አካባቢዎች ዳር ድንበራቸው ተከልሎ የየራሳቸው ሕጋዊ እውቅና ያለው ይዞታ እንዲኖራቸው እና በተግባር በማዕከላዊ (core)፣ መከላከያ (buffer) እና መሸጋገሪያ (transition) ዞን ተለይተው የአስተዳደር ፕላን (Site Mamagement Plan) እንዲዘጋጅላቸው እንዲሁም የአካባቢውን ሕብረተሰብ ባሳተፈ ሁኔታ እንደ አስፈላጊነቱ ከአካባቢው ሕብረተሰብ በሚቀጠሩ የደን ዘቦች ጥበቃ እየተደረገላቸው ከህገወጥ ሠፈራ፣ ከደን ጭፍጨፋ እና ከሌሎች ደኑን ከሚጎዱ ሁኔታዎች እንዲጠበቁ በማድረግ ለተፈለገው ጥቅም እንዲውሉ፤
- ❖ በተፈጥሮ ደን ይዞታዎች ላይ ጥፋት በፈፀሙ አካላት ላይ ፈጣንና ተመጣጣኝ ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ እንዲቻል የፍትህ አካላት ግንዛቤ ዳብሮ ተገቢውን ህጋዊ ድጋፍ የሚያደርጉበት ሁኔታ እንዲመቻች

እርምጃ ሊወሰድ እና ሚኒስቴር መ/ቤቱም በዚህ ዙርያ ቀጣይነት ባለው መልኩ ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል።

124. ከደን የሚገኘውን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታን ከፍ ለማድረግ እና በአሳሳቢ ሁኔታ እየተመናመነ እና እየቀነሰ የሚገኘው የሀገሪቷን የብዝሀ ሕይወት ሀብት ለመጠበቅ

- ❖ በነባር የተፈጥሮ ደን ሀብትነት የተያዙ ይዞታዎች የብዝሀ ሕይወት ስብጥራቸው የተጠበቀ እና የተሻለ እንዲሆን እንዲሁም የነበራቸው የይዞታ መጠን እንዲጨምር በጥናት ላይ የተመሠረተ የሀገር በቀል የዛፍ ችግኝ ተከላ እንዲከናወን
- ❖ በነባር የተፈጥሮ ደን ሀብትነት ከተያዙት እና በመንግስት ጥበቃ እየተደረገላቸው ካሉት በተጨማሪ ተመሳሳይ ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገቡ የተፈጥሮ ደን አካባቢዎችን በጥናት በመለየት ጥበቃ እንዲደረግላቸው፤

በየደረጃው ያሉ ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅባቸውን ተግባር እንዲያከናውኑ ተገቢው ድጋፍ እና ክትትል ሊደረግ ይገባል።

125. በፕሮግራምና ተከታታይነት ባለው መልኩ በጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ዙሪያ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍል፤

- ❖ የደን እሳት አደጋ መከላከልን በተመለከተ ተግባራዊ የግንዛቤ መስጨበጫ ስራ በሰፊው በመሥራት፤
- ❖ ጥናትን መሠረት ባደረገ ሁኔታ በተፈጥሮ ባህሪያቸው እሳትን መከላከል የሚችሉ የዕጽዋት አይነቶችን በመለየት በጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ይዞታ ዙሪያ በሁለትና በሶስት ረድፍ እንዲተከሉ በማድረግ፤ እንዲሁም
- ❖ የደን እሳት ቃጠሎን የመከላከል ተግባርን የሚያስተባብር የደን እሳት መከላከያ ብርጌድ በየደረጃው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ተውጣጥቶ እንቋቋም ሊደረግ የሚቻልበት ሁኔታ በማመቻቸት

በእሳት የሚደርሰውን የደን ቃጠሎ ብዛትና የጉዳት መጠን ለመቀነስ ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

126. በህገ ወጥ መንገድ ለማገዶ እንጨት፣ ለከሰል፣ ለጣውላ ውጤቶች መስርያ ወዘተ ደንን የሚጨፈጭፉ የህብረተሰብ ክፍሎች ቁጥር ለመቀነስ ከማስተማር አና ግንዛቤ ከመስጠቱ እንዲሁም ኅብረተሰቡ ከደን ሀብቱ ሊያገኛቸው የሚችሉ አገግሎቶችን ለመተካት የሚችሉ ሌሎች ዘዴዎች በጥናት እንዲታዩ ከማመቻት በተጨማሪ ቅድሚያ በተሰጣቸው የመንግስት ደን ይዞታዎች መግቢያና መውጫ መንገዶች ላይ የደን ሀብት መቆጥጠርያ ኬላ እንዲቋቋም ሊደረድግ ይገባል፡፡

127. ለደን እና ለሌሎች የልማት ተግባራት የሚሆኑ ቦታዎች የሚመለከታቸውን ባለድርሻ አካላት በየደረጃው በማሳተፍ በቅድሚያ ተጠንተው እንዲለዩ፤ በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ አተገባበር ላይ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለማስተካከልና በሁሉም ባለድርሻ አካላት በኩል ቁርጠኝነት እንዲኖር በማድረግ በልማት ፕሮጀክቶች ላይ የተሻለ የአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ እንደ አስፈላጊነቱ ማከናወን የሚያስችል ሁኔታን ለመፍጠር ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ግንዛቤ እንዲሰጥ ሊደረግ፤ በተለይ ለቡና ልማት የተፈጥሮ ደን ይዞታዎችን ከመስጠት ይልቅ በአጭር ጊዜ ሊደርሱ የሚችሉ የጥላ ዛፎችን የደን ይዞታቸው በተመናመነ ቦታዎች ላይ በመትከል ማልማት የሚቻልበት ልምድ እንዲዳብር ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡ ይህንንም

ለማከናወን የሚችል አደረጃጀት በሚኒስተር መ/ቤቱም ሆነ በየደረጃው በክልል እና በወረዳ ደረጃ እንዲጠናከር ሊደረግ ይገባል፡፡

128. ሚኒስቴር መ/ቤቱ በዕቅድና ተከታታይነት ባለው መልኩ ድጋፍ፣ ቁጥጥርና ክትትል በማድረግ በክልሎችም ሆነ በፌደራል ደረጃ ቅድሚያ በተሰጣቸው የመንግስት ደኖች ዙርያ ለሚኖሩ ህብረተሰብ እና ለሚመለከታቸው ባለደርሻ አካላት ማለትም የመንገድ ስራ ተቋራጮች፣ መብራት ኃይል፣ ፖሊስ፣ ዳኞችና ዓቃቤ ህጎች፣ መንግስታዊ ላልሆኑ ደርጅቶች ወዘተ... ስለ ተፈጥሮ ደን ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ሊሰጥ ይገባል፡፡

129. በተፈጥሮ ደን ሀብቱ ዙሪያ ለሚገኘው ኅብረተሰብ የደን ሀብቱን ይዘት በማይጎዳ መልኩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊያገኝ በሚችልበት ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያገኝ መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት በጅምር ደረጃ እየተከናወነ ያለው የግንዛቤ መስጠት መርሀ ግብር በየደረጃው በሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት በዕቅድ ተካቶ መደበኛና ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚተገበርበት ሁኔታ እንዲመቻች ሊደረግ፤ ይገባል፡፡

130. ከግንዛቤ ማነስ በተለያዩ ስነምህዳር እና ቀጠናዎች የተፈጥሮ ደን ሀብት ላይ ያለአግባብ በሚደርሰው መጠነ ሰፊ ጉዳት የተፈጥሮ ሚዛን እንዳያዛባ ለማድረግ በስፋት ሕብረተሰቡን የማስተማር ስራ የተለያዩ መገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ቀጣይነት እና ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ሊሠራ ይገባል፡፡

131. የሀገራችን የደን ሀብት ለማልማት የሚወጣው ከፍተኛ ወጪ የተፈለገውን ውጤት ለማምጣ በሚችሉ ተገባራት ላይ እየዋለ መሆኑን ለመከታተል እና አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ በወቅቱ ለመውስድ ብሎም በቀጣይ በተሻለ ሁኔታ ተግባራዊ የሚሆን ዕቅድ ለማቀድ እንዲቻል፤

- ❖ የተፈጥሮ ደኑን በተለይም ከፍተኛ የብዝሀ ህይወት ክምችት ይዘው የሚገኙትን ጥብቅ የተፈጥሮ ደን አካባቢዎች ሁኔታን የሚመለከቱ መረጃዎች፣

- በመንግሥት ለደን ልማት ተግባር በተከለሉ አካባቢዎች ላይ በየዓመቱ የተተከሉ ችግኞች አይነት እና መጠን፤ ከተከላ ጊዜአቸው ጀምሮ በየደረጃው የተደረግላቸው እንክብካቤ እና ጥበቃ
- ከተተከሉት ጠቅላላ ችግኞች ውስጥ ምን ያህሉ እንደጸደቁ እና
- በሂደት የሀገሪቱ የተፈጥሮም ሆነ የተተከሉ የደን ሀብቶች እያስገኙ ያለው ጠቀሜታን

የሚያሳዩ መረጃዎች በአግባቡ እንዲጠናቀሩ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ሊዘረጋ እና ከሚመለከታቸው የፌደራል፣ የክልል እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የደን ሀብት የሚመለከቱ አግባብነት ያላቸው መረጃዎች በማያቋርጥና መደበኛ በሆነ መልኩ ልውውጥ ሊደረግ የሚችልበት ሁኔታ እንዲመቻች ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡

132. በደን ወስጥ ቃጠሎ ሲከሰት እሳቱ ከፍተኛ ጉዳት ሳያደርስ በቁጥጥር ስር ለማዋል እንዲቻል የደን እሳት አደጋ ክስተትና መከላከልን በተመለከተ መደበኛ እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ከሀገራዊ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ  የስራ ሂደት ጋር የመረጃ ልውውጥ ስራ ሊከናወን ይገባል፡፡

133. በተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጥናታዊ ጽሁፎች በሰፊው የሚቀርቡ አስተያየቶች ትኩረት ሊሰጣቸው እና የሀገራችን የተፈጥሮ ደንን ከተጋረጠበት ጨርሶ የመጥፋት አደጋ ለመታደግ  የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን በብቃት እና ውጤታማ በሆነ መንገድ  ሊያከናውን የሚችል በተገቢው የአሠራር ስልት እና የሰው ኃይል የተጠናከረ አደረጃጀት በቀጥታ ደንን በማልማት፣ በመጠበቅ እና ዘላቂነትን የተከተለ አጠቃቀም ለመፍጠር በሚደረጉ እንቅስቃሴዎችም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ /በጥምር ግብርና/ ዛፎችን በመትከል የሚደረጉ እንቅስቃሰዎች በባለሙያ በተደገፈ ሁኔታ እንዲከናወኑ ለማድረግ በየደረጃው በሰው ኀይልም ሆነ በቁሳቁስ የተሻለ አደረጃጀት እንዲፈጠር ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡


134. በፌዴራል፣ በክልል እና በወረዳ ደረጃ የሚገኙ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ አካላት የደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን የሚመለከቱ ተግባር እና ኃላፊነቶች በግልፅ እንዲቀመጡ ለማድረግ የሚያግዙ ተጨማሪ አዋጆች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ህጎች፣ ወዘተ… በተገናዘበ ሁኔታ ወጥተው ተግባራዊ የሚሆኑበት መንገድ ሊፈለግ ይገባል፡፡

135. በአገር አቀፍ ደረጃ የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ እና ዘላቂነትን የተከተለ የአጠቃቀም ልምድን ከማዳበር አኳያ ከግል፤ ከማህበር፣ ከድርጅት እና ከባለሀብቶች በኩል የሚጠበቀውን ተሳትፎ ከፍ ለማድረግ ተገቢውን ጥናት ማድረግ እና የደን የይዞታ መጠን እና የአጠቃቀም ሁኔታን የሚያሳዩ መረጃዎችን በማሰባሰብ በአግባቡ እንዲያዙ ሊደረግ ይገባል፡፡

# አባሪዎች

**አባሪ 1.1**


## Percentage of country forest coverage during the 20th Century




Source: Matthias REUSING

**አባሪ 1.2**


## Human Impact on forests in Ethiopia from 1973 to 1990




Source: Matthias REUSING

# የፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር መ/ቤት መዋቅር

## የፌደራል ግብርና ሚኒስቴር መ/ቤት ድርጅታዊ መዋቅር



# የኦዲት መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria)

1. የደን ልማት እና ጥበቃ ፖሊሲ፤ ስራቴጂና አዋጅን ለማስፈጸም የሚረዱ አግባብነት ያላቸው ደንብና መመሪያዎች ሊወጡ እና ተግባራዊ ሊደረጉ ይገባል፡፡
2. የደን ልማት እና ጥበቃ አዋጅ እና ፖሊሲ ላይ የተቀመጡት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተግባር እና ኃላፊነቶች በሚኒስተር መ/ቤቱ ስትራቴጂያዊ እና ዓመታዊ ዕቅድ ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ ሊተገበሩ ይገባል፡፡
3. የሀገሪቱ የመሬት አቀማመጥ እና መሬቱ በደን ቢሸፈን የተሻለ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችልበትን ሁኔታ ያገናዘበ ጥናትን መሠረት ያደረገ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ ሊዘጋጅ እና ይህን ዕቅድ መሠረት በማድረግ ለደን ልማት ሊውሉ የሚገባቸው ቦታዎች ተለይተው ሊታወቁና እንዲያዙ ሊደረግ ይገባል፡፡
4. በመንግስት ጥበቃ ይደረግላቸዋል ከሚባሉት በተጨማሪ በዚህ መልክ ሊያዙ የሚገቡ የተፈጥሮ ደኖች በጥናት እንዲለዩ በማድረግ ጥበቃ እንዲደረግላቸው እንዲሁም በነባር የተፈጥሮ ደን ሀብትነት የተያዙት ይዞታዎች ውስጥ የብዝሀ ሕይወት ስብጥርም ሆነ የይዞታ መጠን እንዲጨምር በጥናት ላይ የተመሠረተ የሀገር በቀል የዛፍ ችግኝ ተከላ እንዲከናወን  ሊደረግ ይገባል፡፡
5. ቅድሚያለተሰጣቸው የሀገሪቱ ጥብቅየተፈጥሮደኖች፤
    i. የአስተዳደር ፕላን (Site Mamagement Plan) እንዲዘጋጅላቸው፣
    ii. ዳርድንበራቸው ተከልሎና ተመዝግቦ በሕግ መሠረት ዕውቅና እንዲያገኙ፣
    iii. እንደ አስፈላጊነቱ በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥታት እንዲተዳደሩ፣
    iv. በየጊዜውየያዙትየመሬትሽፋንእንደ  አካባቢው  ሁኔታውእየታየእንዲያድግ እና
    v. የያዙት የብዝሀሕይወትስብጥርና መጠን ላይ ጥናት በማድረግ በጥናቱ ውጤት መሠረት ተገቢው እርምጃሊወሰድ

    ይገባል፡፡
6. በመንግስት ይዞታ ስር ለሚገኙ ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ከአካባቢው ሕብረተሰብ በሚቀጠሩ የደን ዘቦች ጥበቃ ሊደረግላቸው፤ ከህገ ወጥ ሠፋራ፣ ከደን ጭፍጨፋ እና ከሌሎች ደኑን ከሚጎዱ ሁኔታዎች እንዲጠበቁ በማድረግ ለተፈለገው ጥቅም እንዲውሉ ሊደረግ ይገባል፡፡
7. ጥብቅ የተፈጥሮ ደን ይዞታዎችን ከድንገተኛ እሳት ቃጠሎን ለመከላከል፤
    i. የሚያስተባብር እና ድጋፍ የሚያደርግ የደን እሳት መከላከያ ብርጌድ በየደረጃው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ተውጣጥቶ ሊቋቋም ፡
    ii. በተፈጥሮባህሪያቸውየደንእሳትመከላከልየሚችሉየዕጽዋትአይነቶችበጥብቅየ ተፈጥሮደንሀብቶችይዞታዙሪያበሁለትናበሶስትረድፍሊተከሉ፤

    ይገባል፡

8. በመንግሥት ደኖች መግቢያና መውጫ መንገዶች ላይ የደን ሀብት መቆጣጠሪያ ኬላ ሊቋቋም እና በደን ሀብቱ ላይ የሚደርሰውን ህገወጥ ጭፍጨፋ ለመቆጣጠር ጥረት ሊደረግ ይገባል፡፡
9. ለልማት ተግባራት የሚፈቀዱ ቦታዎች የሀገሪቱ የተፈጥሮ ደን ሀብት ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድሩ ለማድረግ እንዲቻል ለልማት ተግባር የሚሆኑ ቦታዎች በቅድሚያ ተጠንተው እንዲለዩ ሊደረግ ይገባል፡፡
10. ለሚመለከታቸው ወሳኝ ባለድርሻ አካላት በተለይም በተፈጥሮ ደን ሀብቱ ዙሪያ ለሚገኘው ኅብረተሰብ እና መንግስታዊ ለሆኑ አካላት የጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታን በተመለከተ ግንዛቤ እንዲፈጠር ሊደረግ ይገባል፡፡
11. በተፈጥሮ ደን ሀብቱ ዙሪያ የሚገኘው ኅብረተሰብ የደን ሀብቱን ይዘት በማይጎዳ መልኩ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታ ላይ ግንዛቤ ሊያገኝ እና ተጠቃሚም ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡
12. በጥብቅ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ዙሪያ ለሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የደን እሳት መከላከልን በተመለከተ ተግባራዊ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ሊሠራ ይገባል፡፡
13. በተለያዩ የሀገሪቱ ሥነምህዳሮች የሚገኙ የተፈጥሮ ደን ሀብቶች ጠቀሜታ፣ እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ህብረተሰቡ እነዚህን ውድ የሀገር ሀብቶች ቀጣይነትን በተከተለ ሁኔታ እንዴት ሊጠቀም እንደሚገባ የተለያዩ መገናኛ ብዙሀንን በመጠቀም ተከታታይነት ቀጣይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ሊከናወን ይገባል፡፡
14. የደን ሀብት ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀምን የሚመለከቱ መረጃዎችን ከሚመለከታቸው የፌደራል፣ የክልል እና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በተፈለገው አይነት፣ መጠን እና ወቅት ለመለዋወጥ የሚያስችል የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት ሊኖር እና ቀጣይነት ባለው መልኩ እና መደበኛ በሆነ ሁኔታ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
15. በመንግስት ለደን ልማት ተግባር በተከለሉ አካባቢዎች ላይ፣
    i. የሚተከሉት ችግኞች አይነት፣
    ii. ከተተከሉ ችግኞች፣ የጸደቀው መጠን፣
    iii. ከተከላ ጊዜአቸው ጀምሮ በየደረጃው ሊደረግላቸው የሚገባ እንክብካቤ እና ጥበቃ፣
    iv. ለተተከሉበት ዓላማ ስለመዋላቸው ተከታታይነት ያለው ተግባር ለማከናወን የሚያግዝ ጥናት መደረጉን፣
    v. በጥናቱ መሠረት የማስፈጸሚ ዕቅድ መዘጋጀቱ

    በአጠቃላይ ክትትል በማድረግ እያስገኙ ያለው ጠቀሜታን የሚገልጽ መረጃ በመያዝ ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል፡፡
16. የደን• እሳት አደጋ ክስተትና መከላከል የመረጃ ልውውጥ ስራ ከሀገራዊ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የስራ ሂደት ጋር ማድረግ ይገባል፡፡
17. ሚ/ር መ/ቤቱም ሆነ በየደረጃው በተዋረድ በሚገኙ አስፈጻሚ አካላት የደን ልማትና ጥበቃን በተመለከተ በአዋጅ የተጣለበት ኃላፊነት የሚያከናውን አካል ሊዋቀር እና በተገቢው የሰው ኃይልና ቁሳቁስ ተደራጅቶ ፖሊሲውን የማስፈጸም ተግባር ሊያከናውን ይገባል፡፡

18. በፌደራልና በክልሎች በየደረጃው የደን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም መረጃ የሚያቀብሉና አቀነባብረው የሚያሰራጩ አካላት በሰው ኃይልና በዘመናዊ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና መሣሪያ እንዲጠናከሩ ሊደረግ ይገባል፡፡
19. በደን ልማት፣ ጥበቃ እና አጠቃቀም ላይ በግለሰብ፤ በማህበርና በባለሀብቶች ደረጃ የሚደረግ ተሳትፎ እንዲጠናከር ተገቢው ጥረት እና ድጋፍ ሊደረግ እንዲሁም በእነዚህ አካላት ስር የሚገኙ የደን የይዞታዎች መጠንና የአጠቃቀም ሁኔታን የሚያሰዩ መረጃዎችን በማሰባሰብ በአግባቡ እንዲያዙ ሊደረግ ይገባል፡፡

አባሪ 4.1

## ለግብርና ልማት ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ የተሰጠ የመሬት ስፋት እና የወሰዱ ባለሀብቶች ብዛት

| ክልል | የባለሀብት ብዛት | የተሰጠ መሬት ስፋት በሄክታር |
|---|---|---|
| 1. አማራ | 1,290 | 171,772 |
| 2. በደቡብ | 1,408 | 311,502 |
| 3. በትግራይ | 397 | 109,318 |
| 4. በቤንሻንጉል | 306 | 600,254 |
| 5. በአፋር | 56 | 22,365 |
| 6. በኦሮሚያ | 929 | 458,295 |
| 7. በሀረሪ | 37 | 7,428 |
| 8. በሱማሌ | 14 | 9,333 |
| 9. ጋምቤላ | 304 | 399,491 |
| 10. አዲስአበባከተማአስተዳደር | 364 | 17,420 |
| | **5,105** | **2,107,178** |


አባሪ 5.1

## Some of the major recently allotted forest areas for investments in plantation in Sheka Zone

| No. | Investment group name | Area (ha) | *Woreda* | *Kebele* | Remark |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | Azage Anbelo | 80 | Anderacha | Yokchichi | Impl |
| 2 | Abebe Anteneh and Belay Welashe | 1500 | Anderacha | Yokchichi | On proc. |
| 3 | Shishi Opi | 120 | Yeki | Depi | On Proc. |
| 4 | Worku Ado | 170 | Anderacha | Echi | Impl. |
| 5 | Awel Muzein | 160 | Yeki | Alamu | Not Imp. |
| 6. | Denbi Fuafuate | 240 | Yeki | Achane | Impl |
| 7 | Gahiberi | 85 | Yeki | Achane | Impl. |
| 8. | Tesfaye Ibro | 120 | Yeki | Dayi | Impl |
| 9 | Yebora Agri Dev't | 109 | Yeki | Shimerga | Impl. |
| 10 | East African Tea Plantation | 3435 | Masha | Chewaka | Impl. |
| 11 | Gemadro Coffee Plantation | 2295 | Anderacha | Gemadro | Impl. |
| 12 | Gemadro Coffee Plantation II | 1000—2000 | Anderacha | Duwina | On Proc. |
| 13 | Kodo coffee | 70 | Masha | Uwa | Impl. |
| 14 | Shebena coffee | 67 | Anderacha | Shebena | |
| | | | | | |


Source: Sheka Zone Investment Office

አባሪ 5.2




Source: Landuse/Landcover Changes in Andracha and Masha *Woreda*s of Sheka Zone, SNNP Regional State, *Bedru Sherefa*

አባሪ 5.3





| Land cover classes | 1987 | | 2001 | | Difference |
|---|---|---|---|---|---|
| | Area in ha | % | Area in ha | % | |
| Dense closed forest | 55304.5 | 39.0 | 43423.9 | 30.6 | (8.4) |
| Closed forest (disturbed) | 8015.0 | 5.6 | 24369.7 | 17.2 | 11.6 |
| Open forest | 46593.7 | 32.8 | 35077.4 | 24.7 | (8.1) |
| Agric/tree mosaic | 6858.6 | 4.8 | 6675.4 | 4.7 | (0.1) |
| Agricultural lands | 8619.7 | 6.1 | 14672.5 | 10.3 | 4.2 |
| Exposed/cultivated | 1228.3 | 0.9 | 1793.2 | 1.3 | 0.4 |
| Bamboo forest | 13466.5 | 9.5 | 13552.1 | 9.5 | - |
| Wetland | 1890.6 | 1.3 | 1640.7 | 1.2 | (0.1) |
| Tea plantation | | | 758.2 | 0.5 | |

**(Annex 5.1-5.2)**

Source: Landuse/Landcover Changes in Andracha and Masha *Woreda*s of Sheka Zone, SNNP Regional State, *Bedru Sherefa*

# አባሪ 6.1





Source: Landuse/Landcover Changes in Andracha and Masha *Woredas* of Sheka Zone, SNNP Regional State, *Bedru Sherefa*

**Gemadro Kebele (SNNPRS-Sheka Zone)**

Except for high altitude areas dominated by bamboo, the Gemadro Kebele is thought to be influenced by the large estate coffee plantation. To this end, a four period landcover/ landuse assessment was made. A drastic decline in dense forest due to wide spread cutting of large and dense crowned trees, openings of the crowns as opposed to clear cutting manifests deforestation here. It has led to gradual influx of small scale coffee growers in the area following the Gemadro Coffee Plantation. Between 1987 and 2001, there was extensive decline in canopy coverage, as vast area of the Gemadro Kebele was deforested. By 2005 large part of these lands were covered with coffee and shade trees. However, some disturbed closed forest in 2001 has shown a recovery in 2005. (Annex 6.1-6.4)


## አባሪ 6.2




**Spatial representation of periodical landcover classes around Gemadro (1973 and 1987)**


Source: Landuse/Landcover Changes in Andracha and Masha *Woreda*s of Sheka Zone, SNNP Regional State, *Bedru Sherefa*

አባሪ 6.3




Source: Landuse/Landcover Changes in Andracha and Masha *Woredas* of Sheka Zone, SNNP Regional State, *Bedru Sherefa*

## አባሪ 6.4




Source: Landuse/Landcover Changes in Andracha and Masha *Woredas* of Sheka Zone, SNNP Regional State, *Bedru Sherefa*

# IUCN CATEGORIES OF PROTECTED AREAS

| | |
|---|---|
| **Category 1a- Strict Nature Reserve:**<br>Category Ia are strictly protected areas set aside to protect biodiversity and also possibly geological/geomorphological features, where human visitation, use and impacts are strictly controlled and limited to ensure protection of the conservation values. Such protected areas can serve as indispensable reference areas for scientific research and monitoring. | |
| **Category Ia differs from the other categories in the following ways:** | |
| **Category Ib** | Category Ib protected areas will generally be larger and less strictly protected from human visitation than category Ia: although not usually subject to mass tourism they may be open to limited numbers of people prepared for self-reliant travel such as on foot or by boat, which is not always the case in Ia. |
| **Category II** | Category II protected areas usually combine ecosystem protection with recreation, subject to zoning, on a scale not suitable for category I. |
| **Category III** | Category III protected areas are generally centred on a particular natural feature, so that the primary focus of management is on maintaining this feature, whereas objectives of Ia are generally aimed at a whole ecosystem and ecosystem processes. |
| **Category IV** | Category IV protected areas protect fragments of ecosystems or habitats, which often require continual management intervention to maintain. Category Ia areas on the other hand should be largely self-sustaining and their objectives preclude such management activity or the rate of visitation common in category IV. Category IV protected areas are also often established to protect particular species or habitats rather than the specific ecological aims of category Ia. |
| **Category V** | Category V protected areas are generally cultural landscapes or seascapes that have been altered by humans over hundreds or even thousands of years and that rely on continuing intervention to maintain their qualities including biodiversity. Many category V protected areas contain permanent human settlements. All the above are incompatible with category Ia. |
| **Category VI** | Category VI protected areas contain natural areas where biodiversity conservation is linked with sustainable use of natural resources, which is incompatible with category Ia. However large category VI protected areas may contain category Ia areas within their boundaries as part of management zoning. |

Source: IUCN